www.abyssinialaw.com



# የተሻሻለው የ1994 ዓ.ም የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ህገ-መንግሥት

# THE REVISED CONSTITUTION, 2001 OF THE SOUTHERN NATIONS, NATIONALITIES AND PEOPLES' REGIONAL STATE

www.abyssinialaw.com

## አዋጅ ቁጥር ፴፭/፲፱፻፺፬

## የተሻሻለው የ፲፱፻፺፬ ዓ.ም. የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ሕገ መንግሥት ማጽደቂያ አዋጅ

ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ምሥረታ ማግሥት በክልሉ ነዋሪ ሕዝብ ተወካዮች በሐምሌ ተመርጠው ሰኔ ፲፭ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ.ም. በመጀመሪያ የፀደቀው እና እስካሁን ሲሠራበት የቆየውን የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ሕገ መንግሥት በዝርዝር ተመልክቶና በተለይም የክልሉን መንግሥት አንዳንድ የሥልጣን ክፍፍል ግልጽ ተጠያቂነት ያለበትና ቀልጣፋ አገልግሎት ሰጭ አድርጎ ሊያሳይ በሚችል አግባብ የተሟላ አድርጎ ማዘጋጀት ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ምክር ቤት በሥራ ላይ ባለው የክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፩ ንዑስ አንቀጽ ፫/ሀ/ እና ፩፻፲፪ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ከዚህ የሚከተለውን የተሻሻለው የ፲፱፻፺፬ ዓ.ም. የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ሕገ መንግሥት ማጽደቂያ አዋጅ አውጥቷል።

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የተሻሻለው የ፲፱፻፺፬ ዓ.ም የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ሕገ መንግሥት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፴፭/፲፱፻፺፬ ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. **ስለመጽደቁ**

በአዋጅ ቁጥር ፭/፲፱፻፹፯ ዓ.ም. የተደነገገው የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ሕገ መንግሥት ድንጋጌ አቀማመጥ በስፋት ከተዳሰሰ በኋላ የተሻሻለው የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

፫. **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ማጽደቂያ አዋጅ ከዛሬ ህዳር ፳ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ.ም ጀምሮ ይሆናል።

አዋሳ ህዳር ፳ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ.ም

ኃይለማርያም ደሳለኝ

የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል

መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር

## መግቢያ

እኛ የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፦

በጋራ በመፈቃቀድና በእኩልነት ላይ ተመሥርተን በቋቋምነው ክልላችን የጸና የሰላም ዋስትና እንዲኖረን፣ ዲሞክራሲያዊ ማኅበራዊ እድገታችን እንዲፋጠን የራሳችንን ዕድል በራስ የመወሰን መብታችንን ተጠቅመን፣ ቋንቋችንን፣ ባህላችንና አንድነታችንን ይበልጥ ለማጠናከር፣ ማንነታችን ተከብሮ፣ በትግላችንና በክፈልነው መስዋዕትነት የተገኘውን ዲሞክራሲና ሠላም በቀጣይነት ለማረጋገጥ፣

በነዚህ ላይ ያሉትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስችለን የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች መከበራቸውን፣ የጾታ እኩልነት መረጋገጡን፣ ቋንቋዎችና ባህሎቻችን ያለአንዳች ልዩነት በእኩልነት እንዲራመዱ ጽኑ እምነታችን በመሆኑ፤

የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የራሳችን የሆነ አኩሪ ባህልና፣ የራሳችን መልክዓ ምድራዊ አሰፋፈር ያለን፣ በተያያዥ መልክና የሚገናኙ ዘርፈ ብዙ ትስስር ያሏቸው ተሳስረን አብረን የምንኖርበት ክልላችን በመሆኑ፣ ያፈራነው የጋራ ጥቅምና አመለካከት አለን ብለን ስለምናምን፤

ቀጣይ የጋራ እድገታችን መመሥረት ያለበት ካለፈው ጨቋኝ ሥርዓት የወረስነውን የተዛባ ግንኙነት በማረምና የጋራ ጥቅሞቻችንን በማሳደግ ላይ መሆን ስላለበት፤

የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ሕገ መንግሥት ከዚህ [illegible] ዓላማዎችና እሴቶች [illegible] ከ[illegible] በልምድ የተገኘው የክልል ምክር ቤት አባላት አማካይነት [illegible] የጸደቀ የክልሉ ሕገ መንግሥት በ፲፱፻፹፯ ዓ.ም የፀደቀ መሆኑን እያስታወስን፣ ይህ በሥራ ላይ ያለው ሕገ መንግሥታችን ግልጽ ክፍተቶች የታዩበትና የሚያመቻች [illegible] ሥርዓት ተግባራዊ የሆኑ ብዙ ያለው የመንግሥት አካላት አደረጃጀት የሚያመቻች የሚፈለገውን ፈጣን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ማምጣት የሚያስችል በሰፊው እንደገና ተሻሽሎ መውጣት የሚገባው መሆኑን በሙሉ በመረዳት፤

እነሆ ዛሬ ሕዳር ፰ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ.ም በአዋሳ ከተማ በተካሄደው የክልሉ ምክር ቤት ሁለተኛ ዙር አስቸኳይ ጉባኤ ተሻሽሎ የቀረበውን ፲፱፻፹፯ ዓ.ም የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ሕገ መንግሥት ረቂቅ ላይ መክረን አጽድቀነዋል።



www.abyssinialaw.com

## ምዕራፍ አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ ፩
### የክልሉ መንግሥት ሥያሜ

ይህ ህገ መንግሥት የደቡብ ብሔሮች ፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት ዲሞክራሲያዊ አወቃቀርን ያደነግጋል ። በዚህም መሠረት የተቋቋመው መንግሥት "የደቡብ ብሔሮች ፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል" በሚል ሥም ይጠራል።

### አንቀጽ ፪
### የደቡብ ብሔሮች ፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ወሰን

የደቡብ ብሔሮች ፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ወሰን በክልሉ የሚገኙ ዞኖችና ልዩ ወረዳዎች ወሰን ይሆናል።

### አንቀጽ ፫
### ሰንደቅ ዓላማ

የደቡብ ብሔሮች ፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የራሱ ሰንደቅ ዓላማና ዓርማ ይኖረዋል። ሰንደቅ ዓላማው ከላይ ሰማያዊ፣ በመሐሉ ነጭ እና ከታች ቀይ ሆኖ በመሐሉ የክልሉ ዓርማ ጉልቶ ይኖረዋል። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

### አንቀጽ ፬
### የክልሉ መዝሙር

የክልሉ መዝሙር የሕገ መንግሥቱን ዓላማዎች ፣ የክልሉ ሕዝቦች ከሌሎች የኢትዮጵያ ሕዝቦች ጋር በዲሞክራሲ ሥርዓት አብረው ለመኖር ያላቸውን ዕምነት እንዲሁም የክልሉን ሕዝብ የወደፊት የጋራ ዕድል የሚገልፅ ሆኖ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

### አንቀጽ ፭
### ቋንቋ

፩· በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ቋንቋዎች በመንግሥት ዘንድ እኩል ዕውቅና ይኖራቸዋል ።

www.abyssinialaw.com

፪· አማርኛ የክልሉ መንግሥት የሥራ ቋንቋ ይሆናል ።

፫· ዞኖች ወይም ልዩ ወረዳዎች የሥራ ቋንቋ በየምክር ቤቶቻቸው ሊወስኑ ይችላሉ ።

## አንቀጽ ፮
## ርዕሰ ከተማ

የክልሉ መንግሥት ርዕሰ ከተማ አዋሳ ነው።

## አንቀጽ ፯
## የጾታ አገላለጽ

በዚህ ሕገ-መንግሥት ውስጥ ለወንድ ጾታ የተደነገገው የሴቷንም ጾታ ያካትታል ።

# ምዕራፍ ሁለት
# የሕገ መንግሥቱ መሠረታዊ መርሆዎች

## አንቀጽ ፰
## የሕዝብ ወሳኝነት

፩· የደቡብ ብሔሮች ፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የክልሉ መንግሥት የበላይ ሥልጣን ባለቤቶች ናቸው።

፪· የክልሉ ብሔሮች ፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የበላይነት የሚገለጸው በሚመርጧቸው ተወካዮችና ራሳቸው በቀጥታ በሚያደርጉት ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ ነው ።

## አንቀጽ ፱
## የሕገ-መንግሥቱ የበላይነት

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት የበላይነት እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

፩· ይህ ሕገ መንግሥት የክልሉ የበላይ ሕግ ነው ። ማንኛውም ሕግ ፣ ልማዳዊ አሠራር ፣ እንዲሁም የመንግሥታዊ አካል ወይም ባለሥልጣን ውሳኔ ከዚህ ሕገ መንግሥት ጋር የሚቃረን ሆኖ ሲገኝ ተፈጻሚነት አይኖረውም ።

፪· ማንኛውም ሰው ፣ የመንግሥት አካላት ፣ የፖለቲካ ድርጅቶችና



ሌሎች ማህበራት እንዲሁም ባለሥልጣኖቻቸው ይህንን ሕገ መንግሥት የማክበርና እንዲሁም ለሕገ መንግሥቱ ተገዥ የመሆን ኃላፊነት አለባቸው ።

፫· በዚህ ሕገ መንግሥት ከተደነገገው ውጭ በማንኛውም አኳኋን የመንግሥትን ሥልጣን መያዝ የተከለከለ ነው ።

## አንቀጽ ፲
## ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች

፩· ሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶች ከሰው ልጅ ተፈጥሮ የሚመነጩ ፣ የማይጣሱና የማይገፈፉ ናቸው ።

፪· በክልሉ ውስጥ የግለሰቦችና የሕዝቦች ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች የተከበሩ ናቸው ።

## አንቀጽ ፲፩
## የመንግሥትና የሃይማኖት መለያየት

፩· መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው ።

፪· መንግሥታዊ ሃይማኖት አይኖርም።

፫· መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም ። ሃይማኖትም በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም ።

## አንቀጽ ፲፪
## የመንግሥት አሠራርና ተጠያቂነት

፩· የክልሉ መንግሥት አሠራር ለሕዝብ ግልጽ በሆ[illegible] መከናወን አለበት ።

፪· ሕዝቡ በመረጠው ተወካይ ላይ እምነት ባጣ ጊዜ ከቦታው . ይችላል ። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል ።

፫· ማንኛውም ኃላፊ ወይም የሕዝብ ተመራጭ ኃላፊነቱን ሲያጓድል ተጠያቂ ይሆናል ።

www.abyssinialaw.com

## ምዕራፍ ሦስት
## መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች
### አንቀጽ ፲፫
### ተፈጻሚነትና አተረጓጐም

፩. በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የክልሉ መንግሥት አካላት በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተካተቱትን ድንጋጌዎች የማክበርና የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታ አለባቸው።

፪. በዚህ ምዕራፍ የተዘረዘሩት መሠረታዊ የመብቶችና የነፃነቶች ድንጋጌዎች ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሕግጋት ፣ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችና ሰነዶች መርሆዎች ጋር በተጣጣመ መንገድ ይተረጎማሉ ።

## ክፍል አንድ
## ሰብአዊ መብቶች
### አንቀጽ ፲፬
### የሕይወት ፣ የአካል ደህንነትና የነፃነት መብት

ማንኛውም ሰው ሰብአዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነትና የነፃነት መብት አለው።

### አንቀጽ ፲፭
### በሕይወት የመኖር መብት

ማንኛውም ሰው በሕይወት የመኖር መብት አለው ። ማንኛውም ሰው በሕግ በተደነገገ ከባድ የወንጀል ቅጣት ካልሆነ በስተቀር ሕይወቱን አያጣም ።

### አንቀጽ ፲፮
### የአካል ደህንነት መብት

ማንኛውም ሰው በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት አለው ።

### አንቀጽ ፲፯
### የነፃነት መብት

፩. ማንኛውም ሰው በሕግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ነፃነቱን አያጣም ።

፪. ማንኛውም ሰው በሕግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ሊያዝ ፣ ክስ ሳይቀርብበት ወይም ሳይፈረድበት ሊታሰር አይችልም ።

### አንቀጽ ፲፰
### ኢሰብአዊ አያያዝ ስለመከልከሉ

፩. ማንኛውም ሰው ጭካኔ ከተሞላበት ኢሰብአዊ ከሆነ ወይም ክብሩን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የመጠበቅ መብት አለው ።

፪. ማንኛውም ሰው በባርነት ወይም በግዴታ አገልጋይነት ሊያዝ አይችልም ። ለማንኛውም ዓላማ በሰው የመነገድ ተግባር የተከለከለ ነው።

፫. ማንኛውም ሰው በኃይል ተገዶ ወይም ግዴታን ለማሟላት ማንኛውንም ሥራ እንዲሠራ ማድረግ የተከለከለ ነው።

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ "በኃይል ተገዶ ወይም ግዴታን ለማሟላት" የሚለው ሐረግ የሚከተሉትን ሁኔታዎች አያካትትም፡፡

ሀ) ማንኛውም እስረኛ በእስር ባለበት ጊዜ በሕግ መሠረት እንዲሠራ የተወሰነውን ወይም ገደብ ከእስር በተለቀቀበት ጊዜ የሚሠራውን ማንኛውም ሥራ ፣

ለ) ማንኛውም ወታደራዊ አገልግሎት ለመስጠት ሕሊናው የማይ

ፈቅዶለት ሰው በምትኩ የሚሰጥ ማንኛውም አገልግሎት፣

ሐ) የማኅበረሰቡን ሕይወት ወይም ደህንነት የሚያሰጋ አስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ወይም አደጋ በሚያጋጥምበት ጊዜ የሚሰጥ ማንኛውም አገልግሎት፣

መ) በሚመለከተው ሕዝብ ፈቃድ በአካባቢው የሚፈጸምን ማንኛውም የኢኮኖሚና የማኅበራዊ የልማት ሥራ።

## አንቀጽ ፲፱
## የተያዘ ሰው መብት

፩· ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ የተያዘ ሰው የቀረበበት ክስና ምክንያቱ በዝርዝር ወዲያውኑ በሚገባው ቋንቋ እንዲነገረው መብት አለው ።

፪· የተያዘ ሰው ላለመናገር መብት አለው ፤ የሚሰጠው ማንኛውም ቃል ፍርድ ቤት በማስረጃነት ሊቀርብበት እንደሚችል መረዳት በሚችለው ቋንቋ እንደተያዘ ወዲያውኑ ማስገንዘቢያ እንዲሰጠው መብት አለው ።

፫· የተያዘ ሰው በአርባ ስምንት ሰዓታት ውስጥ ፍርድ ቤት የመቅረብ መብት አለው ። ይህም ጊዜ ሰው ከተያዘበት ቦታ ወደ ፍርድ ቤት ለመምጣት አግባብ ባለው ግምት የሚወስደውን ጊዜ አይጨምርም። ወዲያውኑ ፍርድ ቤት እንደቀረበም በተጠረጠረበት ወንጀል ለመታሰር የሚያበቃ ምክንያት ያለ መሆኑ ተለይቶ እንዲገለጽለት መብት አለው ።

፬· የያዘው የፖሊስ መኮንን ወይም የሕግ አስከባሪ በጊዜው ገደብ ፍርድ ቤት በመቅረብ የተያዘበትን ምክንያት ካላስረዳ ፍርድ ቤቱ የአካል ነፃነቱን እንዲያስከብርለት የመጠየቅ ሊጣስ የማይችል መብት አለው። ሆኖም ፍትህ እንዳይጓደል ሁኔታው የሚጠይቅ ከሆነ ፍርድ ቤቱ የተያዘው ሰው በጥበቃ ሥር እንዲቆይ ለማዘዝ ወይም ምርመራ ለማካሄድ ተጨማሪ ጊዜ ሲጠየቅ አስፈላጊ በሆነ መጠን ብቻ ሊፈቅድ ይችላል ። ፍርድ ቤቱ የሚያስፈልገውን ተጨማሪ



www.abyssinialaw.com

የምርመራ ጊዜ ሲወስን ኃላፊ የሆኑት የሕግ አስከባሪ ባለሥልጣኖች ምርመራውን አካሂደው የተያዘው ሰው በተቻለ ፍጥነት ፍርድ ቤት እንዲቀርብ ያለውን መብት የሚያስከብር መሆን አለበት።

፭· የተያዘ ሰው በራሱ ላይ በማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል የእምነት ቃል እንዲሰጥ ወይም ማንኛቸውንም ማስረጃ እንዲያምን አይገደድም። በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረውም።

፮· የተያዘ ሰው በዋስ የመፈታት መብት አለው። ሆኖም በሕግ በተደነገጉ ልዩ ሁኔታዎች ፍርድ ቤት ዋስትና ላለመቀበል ወይም በገደብ መፍታትን ጨምሮ በቂ የሆነ የዋስትና ማረጋገጫ እንዲቀርብ ለማዘዝ ይችላል ።

## አንቀጽ ፳
## የተከሰሰ ሰው መብት

፩· የተከሰሰ ሰው ክስ ከቀረበበት በኋላ ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ በመደበኛ ፍርድ ቤት ለሕዝብ ግልጽ በሆነ ችሎት የመሰማት መብት አለው። ሆኖም የተከራካሪዎችን የግል ሕይወት የሞራል ሁኔታና የአገሪቱ ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል በዝግ ችሎት ሊሰማ ይችላል ።

፪· ክሱ በቂ በሆነ ዝርዝር እንዲነገረውና ክሱን [illegible] መብት አለው።

፫· በፍርድ ሂደት ባለበት ጊዜ በተከሰሰበት [illegible] ያለመቅረብ፣ በምስክርነት እንዲቀርብም [illegible] አለው።

፬· የተከሰሰ ሰው የቀረበበትን ማንኛውንም ማስረጃ የመ[illegible] ምስክሮቹ ቀርበው እንዲሰየሙለት የመጠየቅ መብት አለው።

፭· በመረጠው የሕግ ጠበቃ የመወከል ወይም ጠበቃ የማቆም አቅም በማጣቱ ፍትህ ሊጓደል የሚችልበት ሁኔታ ሲያጋጥም በመንግሥት

ለበሽታ የማግኘት መብት አለው።

፪· ክርክሩ በሚታይበት ፍርድ ቤት በተሰጠበት ትዕዛዝ ወይም ፍርድ ላይ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው።

፫· የፍርድ ሂደት በሚካሄድበት ቋንቋ በማይገባበት ጊዜ በመንግሥት ወጪ ክርክሩ እንዲተረጐምለት የመጠየቅ መብት አለው።

## አንቀጽ ፳፩

### በጥበቃ ሥር ያሉና በፍርድ የታሰሩ ሰው መብት

፩· በጥበቃ ሥር ያሉና በፍርድ የታሰሩ ሰው ሰብአዊ ክብሩን በሚጠብቁ ሁኔታዎች የመያዝ መብት አለው።

፪· ከትዳር ጓደኛው፣ ከቅርብ ዘመዶቹ፣ ከጓደኞቹ፣ ከሃይማኖት አማካሪው፣ ከሐኪሙና ከሕግ አማካሪው ጋር ለመገናኘትና እንዲጎበኙት ዕድል የማግኘት መብት አለው።

## አንቀጽ ፳፪

### የወንጀል ሕግ ወደ ኋላ ተመልሶ የማይሠራ ስለመሆኑ

፩· ማንኛውም ሰው የወንጀል ክስ ሊቀርብበት የተከሰሰበትን ድርጊት በፈጸመበት ጊዜ ድርጊቱ መፈጸሙ ወይም አለመፈጸሙ ወንጀል መሆኑ በሕግ የተደነገገ ካልሆነ በስተቀር ሊቀጣ አይችልም። እንዲሁም ወንጀሉ በተፈጸመ ጊዜ ለወንጀሉ ተፈጻሚ ከነበረው የቅጣት መጣኔ በላይ የከበደ ቅጣት በማንኛውም ሰው ላይ አይወሰንም።

፪· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ድንጋጌ ቢኖርም ድርጊቱ ከተፈጸመ በኋላ የወጣ ሕግ ለተከሳሹ ወይም ለተቀጣው ሰው ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ ከድርጊቱ በኋላ የወጣው ሕግ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

## አንቀጽ ፳፫

### በአንድ ወንጀል ድጋሚ ቅጣት ስለመከልከሉ

ማንኛውም ሰው በወንጀል ሕግና ሥነ ሥርዓት ወይም አግባብ ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት ተከስ የመጨረሻ ውሳኔ ጥፋተኛነቱ በተረጋገጠበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና አይከሰስም ወይም አይቀጣም።

## አንቀጽ ፳፬

### የክብርና የመልካም ስም መብት

፩· ማንኛውም ሰው በማንኛውም ሥፍራ በሰብዓዊ ፍጡርነቱ እውቅና የማግኘት መብት አለው።

፪· ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ ክብሩና መልካም ስሙ የመከበር መብት አለው።

፫· ማንኛውም ሰው የራሱን ስብዕና ከሌሎች ዜጎች መብቶች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ በነፃ የማሳደግ መብት አለው።

## አንቀጽ ፳፭

### የእኩልነት መብት

ሁሉም ሰዎች በሕግ ፊት እኩል ናቸው። በመካከላቸውም ማንኛውም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ በሕግ ዕኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል። በዚህ ረገድ በዘር፣ በብሔር፣ በብሔረሰብ፣ በቀለም፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በማኅበራዊ አመጣጥ፣ በሀብት፣ በትውልድ፣ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ሰዎች ሁሉ ዕኩልና ተጨባጭ የሕግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸው።

## አንቀጽ ፳፮

### የግል ሕይወት የመከበርና የመጠበቅ መብት

፩· ማንኛውም ሰው የግል ሕይወቱ፣ ግላዊነቱ የመከበር መብት አለው።

ይህ መብት መኖሪያ ቤቱ ፣ ሰውነቱና ንብረቱ ከመመርመር እንዲሁም በግል ይዞታው ያለ ንብረት ከመያዝ የመጠበቅ መብትን ያካትታል ።

፪· ማንኛውም ሰው በግል የሚጽፋቸውና የሚጻጻፋቸው ፣ በፖስታ የሚልካቸው ደብዳቤዎች ፣ እንዲሁም በቴሌፎን ፣ በቴሌኮሙኒኬሽንና በኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች የሚያደርጋቸው ግንኙነቶች አይደፈሩም ።

፫· የመንግሥት ባለሥልጣኖች እነዚህን መብቶች የማክበርና የማስከበር ግዴታ አለባቸው ። አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲፈጠሩና ብሔራዊ ደህንነትን ፣ የሕዝብ ሠላምን ፣ ወንጀልን በመከላከል፣ ጤናንና የሕዝብን የሞራል ሁኔታ ለመጠበቅ ወይም የሌሎችን መብትና ነፃነቶች በማስከበር ዓላማዎች ላይ በተመሠረቱ ዝርዝር ሕጎች መሠረት ካልሆነ በስተቀር የእነዚህ መብቶች አጠቃቀም ሊገደብ አይችልም ።

### አንቀጽ ፳፯
### የሃይማኖት ፣ የህሊናና የእምነት ነፃነት

፩· ማንኛውም ሰው የማሰብ ፣ የሕሊና እና የሃይማኖት ነፃነት አለው ። ይህ መብት ማንኛውም ሰው የመረጠውን ሃይማኖት ወይም እምነት መያዝ ወይም የመቀበል ሃይማኖቱንና እምነቱን ለብቻ ወይም ከሌሎች ጋር በመሆን በይፋ ወይም በግል የማምለክ ፣ የመከተል ፣ የመተግበር ፣ የማስተማር ወይም የመግለጽ መብትን ያካትታል ።

፪· በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፲፩(፫) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የሃይማኖት ተከታዮች ሃይማኖታቸውን ለማስፋፋትና ለማደራጀት የሚያስችላቸው የሃይማኖት ትምህርትና የአስተዳደር ተቋማት ለማቋቋም ይችላሉ ።

፫· ማንኛውም ሰው የሚፈልገውን እምነት ለመያዝ ያለውን ነፃነት



www.abyssinialaw.com

በኃይል ወይም በሌላ ሁኔታ በማስገደድ መገደብ ወይም መከልከል አይቻልም ።

፬· ወላጆችና ሌሎች ህጋዊ ሞግዚቶች በእምነታቸው መሠረት የሃይማኖታቸውንና የመልካም ሥነ — ምግባር ትምህርት በመስጠት ልጆቻቸውን የማሳደግ መብት አላቸው ።

፭· ሃይማኖትንና እምነትን የመግለጽ መብት ሊገደብ የሚችለው የሕዝብን ደህንነት ፣ ሠላምን ፣ ጤናን ፣ ትምህርትን ፣ የሕዝብን የሞራል ሁኔታ ፣ የሌሎች ዜጎች መሠረታዊ መብቶች ፣ ነፃነቶችና መንግሥት ከሃይማኖት ነፃ መሆኑን ለማረጋገጥ በሚወጡ ሕጎች ይሆናል ።

### አንቀጽ ፳፰
### በሰብዕና ላይ ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች

ኢትዮጵያ ባፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና በሌሎች የአገሪቱ ሕጎች "በሰው ልጆች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች" ተብለው የተወሰኑትን ወንጀሎች በተለይም የሰው ዘር የማጥፋት ፣ ያለፍርድ የሞት ቅጣት እርምጃ የመውሰድ ፣ በአስገዳጅ የመሰወር ወይም ኢሰብዓዊ የድብደባ ድርጊቶችን በፈጸሙ ላይ ክስ ማቅረብ በይርጋ አይታገድም ። በሕግ አውጭ ሆነ በማንኛውም የመንግሥት አካል ውሳኔዎች በይ በይቅርታ አይታለፉም ።

## ክፍል ሁለት
## ዲሞክራሲያዊ መብቶች

### አንቀጽ ፳፱
### የአመለካከት ሐሳብን በነፃ የመያዝና የመግለፅ መብት

፩· ማንኛውም ሰው ያለምንም ጣልቃ ገብነት የመሰለውን አመለካከት ለመያዝ ይችላል ።

፪· ማንኛውም ሰው ያለምንም ጣልቃ ገብነት ሀሳቡን የመግለጽ ነፃነት አለው ። ይህ ነፃነት በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጭ ወሰን ሳይደረግበት በቃልም ሆነ በጽሑፍ ወይም በህትመት ፣ በሥነ–ጥበብ መልክ ወይም በመረጠው በማንኛውም የማሰራጫ ዘዴ ፣ ማንኛውንም ዓይነት መረጃና ሀሳብን የመሰብሰብ የመቀበልና የማሰራጨት ነፃነቶችን ያካትታል ።

፫· የፕሬስና የሌሎች መገናኛ ብዙሃን እንዲሁም የሥነ – ጥበብ ፈጠራ ነፃነት ተረጋግጧል ።

የፕሬስ ነፃነት በተለይ የሚከተሉትን መብቶች ያጠቃልላል ።

ሀ) የቅድሚያ ምርመራ በማንኛውም መልኩ የተከለከለ መሆኑ ፣

ለ) የሕዝብን ጥቅም የሚመለከት መረጃ የማግኘት ዕድልን ፣

፬· ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ፣ ሀሳቦችና አመለካከቶች በነፃ መንሸራሸራቸውን ለማረጋገጥ ሲባል ፕሬስ በተቋምነቱ የአሠራር ነፃነትና የተለያዩ አስተያየቶች የማስተናገድ ችሎታ እንዲኖረው የሕግ ጥበቃ ይደረግለታል ።

፭· በክልሉ ውስጥ በመንግሥት ገንዘብ የሚካሄድ ወይም በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ያለ መገናኛ ብዙሃን የተለያዩ አስተያየቶችን ለማስተናገድ በሚያስችለው ሁኔታ እንዲመራ ይደረጋል።

፮· እነዚህ መብቶች ገደብ ሊጣልባቸው የሚችለው የሀሳብና መረጃ የማግኘት ነፃነት በአስተሳሰባዊ ይዘቱና ሊያስከትለው በሚችለው አስተሳሰባዊ ውጤት ሊገታ አይገባውም በሚል መርህ ላይ ተመስርተው በሚወጡ ሕጎች ብቻ ይሆናል ። የወጣቶችን ደህንነት፣ የሰውን ክብርና መልካም ስም ለመጠበቅ ሲባል ህጋዊ ገደቦች በእነዚህ መብቶች ላይ ሊደነገጉ ይችላሉ ። የጦርነት ቅስቀሳዎች እንዲሁም ሰብአዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎች በህግ የሚከለከሉ ይሆናሉ ።

፯· ማንኛውም ሰው ከላይ በተጠቀሱት መብቶች አጠቃቀም ረገድ የሚጣሉ ሕጋዊ ገደቦች ጥሶ ከተገኘ በሕግ ተጠያቂ ሊሆን ይችላል ።



www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ ፴

## የመሰብሰብ ፣ ሠላማዊ ሠልፍ የማድረግ ነፃነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት

፩· ማንኛውም ሰው ከሌሎች ጋር በመሆን መሣሪያ ሳይዝ በሠላም የመሰብሰብ ፣ ሠላማዊ ሠልፍ የማድረግ ነፃነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው ። ከቤት ውጭ የሚደረጉ ስብሰባዎችና ሠላማዊ ሠልፎች በሚንቀሳቀሱባቸው ቦታዎች በሕዝብ እንቅስቃሴ ላይ ችግር እንዳይፈጥሩ ለማድረግ ወይም በመካሄድ ላይ ያለ ስብሰባ ወይም ሠላማዊ ሠልፍ ሠላምን ፣ ዲሞክራሲያዊ መብቶችና የሕዝብን የሞራል ሁኔታ እንዳይጣሱ ለማስጠበቅ አግባብ ያላቸው ሥርዓቶች ሊደነገጉ ይችላሉ ።

፪· ይህ መብት የወጣቶችን ደህንነት ፣ የሰውን ክብርና መልካም ስምን ለመጠበቅ ፣ የጦርነት ቅስቀሳዎች እንዲሁም ሰብአዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎችን ለመከላከል ሲባል በሚወጡ ሕጎች መሠረት ተጠያቂ ከመሆን አያድንም።

## አንቀጽ ፴፩

## የመደራጀት መብት

ማንኛውም ሰው ለማንኛውም ዓላማ በማህበር የመደራጀት መብት አለው። ሆኖም አግባብ ያለውን ሕግ በመጣስ ወይም ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን በሕገ ወጥ መንገድ ለማፍረስ የተመሠረቱ ወይም የተጠቀሱትን ተግባራት የሚያራምዱ ድርጅቶች የተከለከሉ ይሆናሉ ።

## አንቀጽ ፴፪

## የመዘዋወር ነፃነትና የመኖሪያ ቦታ የመመሥረት መብት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፴፪ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ፣ ማንኛውም የክልሉ ነዋሪ ወይም በሕጋዊ መንገድ በክልሉ ውስጥ የሚገኝ ሰው በመረጠው የክልሉ አካባቢ የመዘዋወርና የመኖሪያ ቦታ

የመመሥረት፣ ሠርቶ የመኖር፣ ንብረት የማፍራት እና የመያዝ እንዲሁም በፈለገ ጊዜ ከክልሉ የመውጣት መብት አለው።

## አንቀጽ ፴፫
## በሕዝባዊና መንግሥታዊ ሥራዎች የመሳተፍ መብት

የክልሉን፣ የዞኑን ወይም የልዩ ወረዳውን የሥራ ቋንቋ የሚያውቅ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በማንኛውም የክልሉ ሕዝባዊና መንግሥታዊ ሥራዎች ተመርጦ ወይም ተመድቦ የመሥራት መብት አለው።

## አንቀጽ ፴፬
## የጋብቻ፣ የግልና የቤተሰብ መብቶች

፩· ይችላል በሕግ ከተወሰነው የጋብቻ ዕድሜ የደረሱ ወንዶችና ሴቶች በዘር፣ በብሔር፣ ብሔረሰብ፣ በሃይማኖት ወይም በሌሎች ምክንያቶች ልዩነት ሳይደረግባቸው የማግባትና ቤተሰብ የመመሥረት መብት አላቸው። በጋብቻ አፈፃፀም፣ በጋብቻ ዘመንና በፍቺ ጊዜ እኩል መብት አላቸው። በፍችም ጊዜ የልጆች መብትና ጥቅም እንዲከበር የሚያደርጉ ድንጋጌዎች ይደነገጋሉ።

፪· ጋብቻ በተጋቢዎች ነፃና ሙሉ ፈቃደኝነት ላይ ብቻ ይመሠረታል።

፫· ቤተሰብ የሕብረተሰብ የተፈጥሮ መሠረታዊ መነሻ ነው። ከሕብረተሰቡና ከመንግሥት ጥበቃ የማግኘት መብት አለው።

፬· በሕግ በተለይ በሚዘረዘረው መሠረት በሃይማኖቶች፣ በባህል ሥርዓቶች ላይ ተመሥርተው ለሚፈፀሙ ጋብቻዎች እውቅና የሚሰጥ ሕግ ሊወጣ ይችላል።

፭· ይህ ሕገ መንግሥት የግልና የቤተሰብ ሕግን በተመለከተ በተከራካሪዎች ፈቃድ፣ በሃይማኖቶች ወይም በባሕሎች ሕጎች መሠረት መዳኘትን አይከለክልም። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

## አንቀጽ ፴፭
## የሴቶች መብት

፩· ሴቶች ይህ ሕገ መንግሥት በአረጋገጣቸው መብቶችና ጥበቃዎች



www.abyssinialaw.com

በመጠቀም ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው ።

፪· ሴቶች በዚህ ሕገ መንግሥት በተደነገገው መሠረት በጋብቻ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው።

፫· ሴቶች በበታችነትና በልዩነት ሲታዩ በመቆየታቸው ምክንያት የደረሰባቸውን ጠባሳ ከግምት ውስጥ በማስገባት ይህ የታሪክ ጠባሳ እንዲታረምላቸው በተጨማሪ የድጋፍ እርምጃዎች ተጠቃሚ የመሆን መብት አላቸው። ከዚህ አኳያ የሚወሰዱት እርምጃዎች ዓላማ በፖለቲካዊ፣ በማኅበራዊና በኢኮኖሚያዊ እንዲሁም በመንግሥትና በግል ተቋሞች ውስጥ ሴቶች ከወንዶች ጋር በእኩልነት ተወዳዳሪና ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ እንዲቻል ልዩ ትኩረት ለመስጠት ነው።

፬· ሴቶች ከጎጂ ልማድ ተፅዕኖ ለመላቀቅ ያላቸውን መብት መንግሥት ማስከበር አለበት ። ሴቶችን የሚጨቁኑ ወይም በአካላቸው ወይም በአዕምሮአቸው ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ሕጎች ፣ ወጎችና ልማዶች የተከለከሉ ናቸው ።

፭· ሴቶች የቅጥር ፣ የሥራ ዕድገት ፣ የዕኩል ክፍያና ጡረታን የማስተላለፍ ዕኩል መብት አላቸው ።

፮· በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ወይም በግል ድርጅቶች ተቀጥረው የሚሠሩ ሴቶች፡-

ሀ) የወሊድ ፈቃድ ከሙሉ የደመወዝ ክፍያ ጋር የማግኘት መብት አላቸው ፤ የወሊድ ፈቃድ ርዝመት ሴቷ የምትሠራውን ሥራ ሁኔታ ፣ የሴቷን ጤንነት ፣ የሕፃኑንና የቤተሰቡን ደህንነት ከግምት ውስጥ በማስገባት በሕግ ይወሰናል ፤

ለ· የወሊድ ፈቃድ በሕግ በሚወሰነው መሠረት ከሙሉ የደመወዝ ክፍያ ጋር የሚሰጥ የእርግዝና ፈቃድን ሊጨምር ይችላል ።

፯· ሴቶች በእርግዝናና በወሊድ ምክንያት የሚደርስባቸውን ጉዳት ለመከላከልና ጤንነታቸውን ለማስጠበቅ የሚያስችል የቤተሰብ ምጣኔ ትምህርት መረጃና አቅም የማግኘት መብት አላቸው ።

www.abyssinialaw.com

፰· ሴቶች ንብረት የማፍራት የማስተዳደር ፣ የመቆጣጠር ፣ የመጠቀምና የማስተላለፍ መብት አላቸው ። በተለይ መሬትን በመጠቀም ፣ በማስተላለፍ ፣ በማስተዳደርናበመቆጣጠር ረገድ ከወንዶች ጋር ዕኩል መብት አላቸው ። እንዲሁም ውርስን በሚመለከት በዕኩልነት የመታየት መብት አላቸው ።

፱· ሴቶች በክልሉ የልማት ፖሊሲዎች ዕቅድና በፕሮጀክቶች ዝግጅትና አፈጻጸም በተለይ የሴቶችን ጥቅም በሚነኩ ፕሮጀክቶች ላይ ሃሳባቸውን በተሟላ ሁኔታ እንዲሰጡ የመጠየቅ መብት አላቸው ።

## አንቀጽ ፴፮
## የሕፃናት መብት

፩· ማንኛውም ሕፃን የሚከተሉት መብቶች አሉት፦

ሀ· በሕይወት የመኖር ፤

ለ· ስምና ዜግነት የማግኘት ፤

ሐ· ወላጆችን ወይም በሕግ የማሳደግ መብት ያላቸው ሰዎች የማወቅና የእነሱንም እንክብካቤ የማግኘት ፤

መ· ጉልበቱን ከሚበዘብዙ ልማዶች ፤ የመጠበቅ ፣ በትምህርቱ ፣ በጤናውና በደኅንነቱ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ሥራዎች እንዲሠራ ያለመገደድ ወይም ከመሥራት የመጠበቅ ፣

ሠ· በትምህርት ቤቶች ወይም በሕፃናት ማሳደጊያ ተቋሞች ውስጥ በአካሉ ላይ ከሚፈፀም ወይም ከጭካኔና ኢሰብአዊ ከሆነ ቅጣት ነፃ የመሆን ።

፪· ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ በመንግሥታዊ ወይም በግል የበጎ አድራጎት ተቋሞች ፣ በፍርድ ቤቶች ፣ በአስተዳደር ባለሥልጣኖች ፣ ወይም በሕግ አውጪ አካላት የሕፃናት ደህንነት በቀደምትነት መታሰብ አለበት ።

፫· ወጣት አጥፊዎች በማረሚያ ወይም በመቋቋሚያ ተቋሞች የሚገኙ በመንግሥት ዕርዳታ የሚያድጉ ወጣቶች በመንግሥት ወይም የግል



እንክብካቤ ተቋሞች ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች ከአዋቂዎች ተለይተው መያዝ አለባቸው ።

፬· ከጋብቻ ውጭ የተወለዱ ሕፃናት በጋብቻ ከተወለዱ ሕፃናት ጋር እኩል መብት አላቸው ።

፭· መንግሥት ለእጓለማውታን ልዩ ጥበቃ ያደርግላቸዋል ። በጉዲፈቻ የሚያድጉበትን ሥርዓት የሚያመቻቹና የሚያስፋፉ እንዲሁም ደህንነታቸውንና ትምህርታቸውን የሚያራምዱ ተቋሞች እንዲመሠረቱ ያበረታታል ።

## አንቀጽ ፴፯
## ፍትህ የማግኘት መብት

፩· ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከተው ውሳኔ ወይም ፍርድ፣

ሀ) ማንኛውም ማኅበር የአባላቱን የጋራ ወይም የግል ጥቅም በመወከል፤

ለ) ማንኛውም ቡድን ወይም ተመሳሳይ ጥቅም ያላቸውን ሰዎች የሚወክል ግለሰብ ወይም የቡድን አባል የመጠየቅና የማግኘት መብት አለው።

## አንቀጽ ፴፰
## የመምረጥና የመመረጥ መብት

፩· ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ፣ በዘር፣ በቀለም፣ በብሔር፣ በብሔረሰብ፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በኃይማኖት፣ ብፖለቲካ ወይም በሌላ አመለካከት ወይም አቋም ላይ የተመሠረተ ልዩነት ሳይደረግበት የሚከተሉት መብቶች አሉት፦

ማግኘት፡ ሲረጋገጥና ጥያቄው በጽሑፍ ለክልሉ ምክር ቤት ሲቀርብ፣

ለ) ጥያቄው የቀረበለት የክልል ምክር ቤት ጥያቄው በደረሰው በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለጠየቀው ብሔር፣ ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ሕዝበ ውሣኔ ሲያደራጅ፣

ሐ) ክልል የመመሥረት ጥያቄው በብሔሩ፣ በብሔረሰቡ ወይም ሕዝቡ ሕዝበ ውሣኔ በአብላጫ ድምጽ ሲደገፍ፣

መ) የክልሉ ምክር ቤት ሥልጣኑን ለጠየቀው ብሔር፣ ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ሲያስረክብ፣

ሠ) በሕዝበ ውሣኔ የሚፈጠረው አዲስ ክልል ጥያቄ ማቅረብ ሳያስፈልገው በቀጥታ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አባል ሲሆን ነው።

፭· በዚህ ሕገ መንግሥት ውስጥ "ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ" ማለት ቀጥሎ የተገለጹትን ባህርያት የሚያሳይ ማኅበረሰብ ነው። ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንፀባርቅ ባሕል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች ያላቸው፣ ሊግባቡበት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ ያላቸው፣ የጋራ ወይም የተዛመደ ሕልውና አለን ብለው የሚያምኑ የሥነ ልቦና አንድነት ያላቸውና በአብዛኛው በተያያዘ መልክዓ ምድር የሚኖሩ ናቸው።

## አንቀጽ ፵
## የንብረት መብት

፩· ማንኛውም በክልሉና ከክልሉ ውጭ የሚኖር ኢትዮጵያዊ የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ ይከበርለታል፤ ይህ መብት የሕዝብን ጥቅም ለመጠበቅ በሌላ ሁኔታ በሕግ እስካልተወሰነ ድረስ ንብረት የመያዝና በንብረት የመጠቀም፣ ወይንም የሌሎችን ዜጎች መብቶች እስካልተቃረኑ ድረስ ንብረት የመሸጥ፣ የማውረስ ወይም በሌላ መንገድ የማስተላለፍ መብቶችን ያካትታል።



www.abyssinialaw.com

፪· ለዚህ አንቀጽ ዓላማ "የግል ንብረት" ማለት ማንኛውም በክልሉና ከክልሉ ውጭ የሚኖር ኢትዮጵያዊ ወይም ሕጋዊ ሰውነት በሕግ የተሰጣቸው አገር አቀፋዊ ወይም ክልላዊ ማኅበራት፣ ወይም አግባብ ባላቸው ሁኔታዎች በሕግ በተለየ በጋራ የንብረት ባለቤቶች እንዲሆኑ የተፈቀደላቸው ማኅበረሰቦች፣ በጉልበታቸው በፈጠራ ችሎታቸው፣ ወይም በካፒታላቸው፣ የአፈሩት ተጨባጭ የሆነና የተጨባጭነት ጠባይ ሳይኖረው ዋጋ ያለው ውጤት ነው።

፫· የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግሥትና የሕዝብ ብቻ ነው። መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የክልሉ ሕዝብ የጋራ ንብረት ነው።

፬· የክልሉ አርሶ አደሮች መሬት በነፃ የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመፈናቀል መብታቸው የተከበረ ነው። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

፭· በክልሉ የሚገኙ አርብቶ አደሮች ለግጦሽም ሆነ ለእርሻ የሚጠቀሙበት መሬት በነፃ የማግኘት፣ የመጠቀምና ከመሬታቸው ያለመፈናቀል መብት አላቸው። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

፮· የመሬት ባለቤትነት የሕዝብ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መንግሥት ለግል ባለሀብቶች በሕግ በሚወሰን ክፍያ በመሬት የመጠቀም መብታቸውን ያስከብርላቸዋል። ዝርዝሩም በሕግ ይወሰናል።

፯· ማንኛውም በክልሉና ከክልሉ ውጭ የሚኖር ኢትዮጵያዊ በጉልበቱ ወይም በገንዘቡ በመሬት ላይ ለሚገነባው ቋሚ ንብረት ወይም ለሚያደርገው ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት አለው። ይህ መብት የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ የማውረስ፣ የመሬት ተጠቃሚነቱ ሲቋረጥ ንብረቱን የማንሳት፣ ባለቤትነቱን የማዛወር ወይም የካሣ ክፍያ የመጠየቅ መብት ያካትታል። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

፰· የግል ንብረት ባለቤትነት መብት እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መንግሥት ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተመጣጣኝ ካሳ በቅድሚያ በመክፈል የግል ንብረቱን ለመውሰድ ይችላል።

## አንቀጽ ፴፩
## የኢኮኖሚ የማኅበራዊና የባህል መብቶች

፩· ማንኛውም የክልሉ ነዋሪና በክልሉ ውስጥ ለመኖር የሚፈልግ ኢትዮጵያዊ በክልሉ ውስጥ በማንኛውም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመሠማራትና ለመተዳደሪያው የመረጠውን ሥራ የመሥራት መብት አለው።

፪· ማንኛውም የክልሉ ነዋሪ መተዳደሪያውን፣ ሥራውንና ሙያውን የመምረጥ መብት አለው።

፫· የክልሉ ነዋሪዎች ሁሉ በመንግሥት ገንዘብ በሚካሄደው ማኅበራዊ አገልግሎት በእኩልነት የመጠቀም መብት አላቸው።

፬· የክልሉ መንግሥት የጤና፣ የትምህርትና ሌሎች ማኅበራዊ አገልግሎቶችን ለሕዝብ ለማቅረብ በየጊዜው እየጨመረ የሚሄድ ሀብት ይመድባል።

፭· የክልሉ መንግሥት የአካልና የአዕምሮ ጉዳተኞችን፣ አረጋዊያንና ያለወላጅ ወይም ያለአሳዳጊ የቀሩ ሕፃናትን ለማቋቋምና ለመርዳት የክልሉ ኢኮኖሚ አቅም በፈቀደው ደረጃ እንክብካቤ ያደርጋል።

፮· የክልሉ መንግሥት ለሥራ አጦችና ለችግረኞች ሥራ ለመፍጠር የሚያስችል ፖሊሲ ይከተላል፣ እንዲሁም በሚካሄደው የሥራ ዘርፍ ውስጥ የሥራ ዕድል ለመፍጠር የሥራ ፕሮግራሞችን ያወጣል፣ ፕሮጀክቶችን ያካሂዳል።

፯· የክልሉ መንግሥት የክልሉ ነዋሪዎች ጠቃሚ ሥራ የማግኘት ዕድላቸው እየሰፋ እንዲሄድ ለማድረግ አስፈላጊ እርምጃዎችን ይወስዳል።

፰· ገበሬዎች እና አርብቶ አደሮች በየጊዜው እየተሻሻለ የሚሄድ ኑሮ ለመኖር የሚያስችላቸውንና ለብሔራዊ ሀብት ካደረጉት የምርት አስተዋጽኦ ጋር ተመጣጣኝ ዋጋ ለምርት ውጤቶቻቸው የማግኘት መብት አላቸው። መንግሥት የኢኮኖሚ የማኅበራዊና የልማት



www.abyssinialaw.com

ፖሊሲዎችን በሚተልምበት ጊዜ በዚህ ዓላማ መመራት አለበት።

፱· የክልሉ መንግሥት የባህልና የታሪክ ቅርሶችን የመንከባከብና ለሥነ ጥበብና ለስፖርት መስፋፋት አስተዋጽኦ የማድረግ ኃላፊነት አለበት።

## አንቀጽ ፴፪
## የሠራተኛ መብት

፩· የፋብሪካና የአገልግሎት ሠራተኞች፣ የእርሻ ሠራተኞች፣ ገበሬዎች፣ ሌሎች የገጠር ሠራተኞች፣ ከተወሰነ የኃላፊነት ደረጃ በታች ያሉና የሥራ ጠባያቸው የሚፈቅድላቸው የመንግሥት ሠራተኞች፣

ሀ) የሥራና የኢኮኖሚ ሁኔታዎችን ለማሻሻል በማኅበር የመደራጀት መብት አላቸው። ይህ መብት የሠራተኛ ማኅበራትንና ሌሎች ማኅበራትን የማደራጀት፣ ከአሠሪዎችና ጥቅማቸውን ከሚነኩ ሌሎች ድርጅቶች ጋር የመደራደር መብትን ያካትታል፤

ለ) በንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከቱት የሠራተኛ ክፍሎች ሥራ የማቆምን ጨምሮ ቅሬታ የማሰማት መብት አላቸው፤

ሐ) በንዑስ አንቀጽ (ሀ) እና (ለ) መሠረት እውቅና ባገኙት መብቶች ለመጠቀም የሚችሉት ሠራተኞች በህግ ይወሰናሉ፤

መ. ሴቶች ሠራተኞች ለተመሳሳይ ሥራ ተመሳሳይ ክፍያ የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ ነው።

፪· ሠራተኞች በአግባቡ የተወሰነ የሥራ እረፍት፣ የመዝናኛ ጊዜ በየጊዜው ከክፍያ ጋር የሚሰጡ የእረፍት ቀኖች፣ ደመወዝ የሚከፈልባቸው የሕዝብ በዓላት እንዲሁም ጤናማና አደጋ የማያደርስ የሥራ አካባቢ የማግኘት መብት አላቸው።

፫· እነዚህን መብቶች ተግባራዊ ለማድረግ የሚወጡ ሕጎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት እውቅና ያገኙትን መብቶች ሳይቀንሱ የተጠቀሱት ዓይነት የሠራተኛ ማኅበራት ስለሚቋቋሙበትና የጋራ ድርድር ስለሚካሄድበት ሥርዓት ይደነግጋል።

## አንቀጽ ፵፫
## የልማት መብት

፩· የክልሉ ነዋሪዎች የኑሮ ሁኔታዎችን የማሻሻልና የማያቋርጥ እድገት የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ ነው።
፪· የክልሉ ነዋሪዎች በብሔራዊ ልማት የመሳተፍ በተለይም አባል የሆኑበትን ማኅበረሰብ በሚመለከቱ ፖሊሲዎችንና ፕሮጀክቶች ላይ ሃሳባቸውን እንዲሰጡ የመጠየቅ መብት አላቸው።
፫· የልማት እንቅስቃሴ ዋና ዓላማ የክልሉን ነዋሪዎች እድገትን መሠረታዊ ፍላጎት ማሟላት ይሆናል።

## አንቀጽ ፵፬

## የአካባቢ ደኅንነት መብት

፩· የክልሉ ነዋሪዎች ንፁህና ጤናማ በሆነ አካባቢ የመኖር መብት አላቸው።
፪· የክልሉ መንግሥት በሚያካሂዳቸው ፕሮግራሞች ምክንያት የተፈናቀሉ ወይም ኑሮአቸው የተነካባቸው ሰዎች ሁሉ በመንግሥት በቂ እርዳታ፣ ወደ ሌላ አካባቢ መዘዋወርን ጨምሮ ተመጣጣኝ የሆነ ገንዘብ ወይም ሌላ አማራጭ ማካካሻ የማግኘት መብት አላቸው።

# ምዕራፍ አራት
# የክልሉ መንግሥት አደረጃጀትና የሥልጣን ክፍፍል
## አንቀጽ ፵፭
## የክልሉ አስተዳደር እርከኖች

፩· የክልሉ መንግሥት፣ በዞኖች በልዩ ወረዳዎች፣ በወረዳዎችና በቀበሌዎች የተዋቀረ ነው። ይሁን እንጂ የክልሉ ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሌሎች የአስተዳደር እርከኖችን ሊያዋቅርና



www.abyssinialaw.com

ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን ይችላል።
፪· በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች አሰፋፈራቸውን፣ ቋንቋቸውን፣ ማንነታቸውን እና ፈቃዳቸውን መሠረት በማድረግ የሚቋቋሙ የየራሳቸው የዞን ወይም የልዩ ወረዳ አስተዳደር ይኖራቸዋል።
፫· በክልሉ የሚገኙ ከተሞች የየራሳቸው አስተዳደር ይኖራቸዋል። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

## አንቀጽ ፵፮
## የክልሉ መንግሥት የሥልጣን አካላት

፩· የክልሉ መንግሥት ህግ አውጭ አካል የክልሉ ምክር ቤት ሲሆን የክልሉ መንግሥት ከፍተኛ የሥልጣን አካል ሆኖ ተጠሪነቱም ለወከለው ሕዝብ ነው።
፪· የክልሉ ከፍተኛ የሕግ አስፈጻሚ አካል የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሲሆን ተጠሪነቱም ለክልሉ ምክር ቤት ነው።
፫· የክልል የዳኝነት ሥልጣን የክልሉ ፍርድ ቤቶች ብቻ ነው።

## አንቀጽ ፵፯
## የክልሉ መንግሥት ሥልጣንና ተግባር

፩· በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ውስጥ በውል ተለይተው ለፌዴራሉ መንግሥት ወይም ለፌዴራሉ መንግሥትና ለክልሉ በጋራ ከተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ውጭ ያሉ ማናቸውም ሥልጣንና ተግባር የክልሉ መንግሥት ሥልጣንና ተግባር ይሆናል።
፪· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ክልል መንግሥቱ፦
   ሀ) የክልሉን የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ልማት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና

www.abyssinialaw.com

ዕቅድ ያወጣል፣ ያስፈጽማል፤

ለ) የክልሉን ሕገ መንግሥትና ሌሎች ሕጎችን ያወጣል፣ ያስፈጽማል፤

ሐ) የፌዴራሉ መንግሥት በሚያወጣው ሕግ መሠረት መሬትንና የተፈጥሮ ሀብትን ያስተዳድራል፤

መ) ራስን በራስ ማስተዳደርን ዓላማ ያደረገ ክልላዊ መስተዳድር ያዋቅራል፣ የሕግ የበላይነት የሰፈነበት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ይገነባል። የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥትና ይህንን ሕገ መንግሥት ይጠብቃል፣ ይከላከላል።

ሠ) የክልሉን መስተዳድር ሠራተኞች አስተዳደርና የሥራ ሁኔታዎች በተመለከተ ሕግ ያወጣል፣ ያስፈጽማል፣ ይህን በሚያስፈጽምበት ጊዜ የሀገሪቱን የትምህርት፣ የሥልጠናና የልምድ መመዘኛዎች ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል።

ረ) የክልሉን ፖሊስ ኃይል ያደራጃል፣ ይመራል፣ የክልሉን ሰላምና ፀጥታ ይጠብቃል፤

ሰ) የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፪ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና የዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፪ ድንጋጌዎች እንደተጠበቀ ሆነው በሕግ መሠረት ምህረት ያደርጋል።

ሸ) ለክልሉ በተወሰነ የገቢ ምንጭ ላይ ግብርና ሌሎች ታክሶችን ይጥላል፣ ይሰበስባል፣ የክልሉን መንግሥት በጀት ያወጣል፣ ያስፈጽማል፣

ቀ) በክልል መስተዳድርና በድርጅት ተቀጣሪዎች ላይ የሥራ ግብር ይጥላል፣ ይሰበስባል፤

በ) የመሬት መጠቀሚያ ክፍያ ይወስናል፣ ይሰበስባል፤

ተ) የእርሻ ሥራ ግብር ይጥላል፣ ይሰበስባል፤

ቸ) በክልሉ በግል ባለቤትነት ሥር ካሉ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ይጥላል፣ ይሰበስባል፤ በክልል መስተዳድሩ ባለቤትነት ሥር ባሉ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች ላይ ኪራይ ያስከፍላል፤

ኀ) በክልል መስተዳድር ባለቤትነት ከሚገኙ ድርጅቶች ላይ የንግድ ትርፍ፣ የሥራ ግብርና የሽያጭና ኤክሳይዝ ታክስ ይጥላል፣ ይሰበስባል፤

ነ) በክልሉ በሚገኙ ግለሰብ ነጋዴዎች ላይ የንግድ ትርፍ ግብርና የሽያጭ ታክስ ይጥላል ይሰበስባል፤

ኘ) በክልሉ ውስጥ በውሃ ላይ በሚደረግ ትራንስፖርት በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ይጥላል ይሰበስባል፤

አ) በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፺፰ ንዑስ አንቀጽ ፫ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በማዕድን ሥራዎች ላይ የማዕድን ገቢ ግብር የሮያሊቲና የመሬት ኪራይ ክፍያዎችን ይጥላል፣ ይሰበስባል፤

ከ) ከፌዴራሉ መንግሥት ጋር፦

ሀ) በጋራ ከሚያቋቁማቸው የልማት ድርጅቶች የሚገኘውን የንግድ ትርፍ ግብር፣ የሥራ ግብር፣ የሽያጭና የኤክሳይዝ ታክስ በሕጉ መሠረት ይካፈላል፤

ለ) ከድርጅቶቹ የንግድ ትርፍ ላይና ከባለአክሲዮኖች የትርፍ ድርሻ ላይ ግብርና የሽያጭ ታክስ በሕጉ መሠረት ይካፈላል።

ሐ) ከከፍተኛ የማዕድን ሥራዎችና ከማንኛውም የፔትሮሊየምና የጋዝ ሥራዎች የሚገኘውን የገቢ ግብርና የሮያሊቲ ክፍያዎች በሕጉ መሠረት ይካፈላል፤

ኸ) በክልል መስተዳድር አካላት ከሚሰጡ ፈቃዶችና አገልግሎቶች የሚመነጩ ክፍያዎችን ይወስናል፣ ይሰበስባል፤

ወ) ከደን የሚገኝ የሮያሊቲ ክፍያን ይወስናል፣ ይሰበስባል፤

ዐ) በክልሉ ውስጥ ማናቸውም የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም

የሕዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያወጣል።

፫· የክልሉ መንግሥት በዚህ አንቀጽ ከተጠቀሰው ሥልጣንና ተግባር ውስጥ እንደአስፈላጊነቱ ለበታች አስተዳደር እርከኖች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

## ምዕራፍ አምስት

## ስለ ክልሉ መንግሥት ምክር ቤቶች

### አንቀጽ ፵፰

የክልሉ መንግሥት ሁለት ምክር ቤቶች ይኖሩታል። እነዚህም የክልሉ ምክር ቤትና የብሔረሰቦች ምክር ቤት ናቸው።

### አንቀጽ ፵፱

### የምክር ቤቶቹ የወል ድንጋጌዎች

፩· እያንዳንዱ ምክር ቤት፡-

ሀ) የራሱን አፈ ጉባዔና ምክትል አፈጉባዔ በምክር ቤት ውስጥ አብላጫው ድምጽ ባገኘው የፖለቲካ ድርጅት ወይም የፖለቲካ ድርጅቶች አቅራቢነት በምርጫ ይሰይማል። ለሥራ የሚያስፈልጉትን ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎችን ያዋቅራል፤

ለ) የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል። ምክር ቤቱ ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ ይሰበሰባል።

፪· የእያንዳንዱ ምክር ቤት አባላት፡-

ሀ) በምክር ቤቱ ውስጥ በሚሰጠው ድምጽ ወይም አስተያየት ምክንያት አይከሰስም፣ አስተዳደራዊ እርምጃ አይወሰድበትም፤

ለ) ከባድ ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፍንጅ ካልተያዘ በስተቀር ያለምክር ቤቱ ፈቃድ አይያዝም፣ በወንጀል አይከሰስም፤

ሐ) የመረጠውን ሕዝብ አመኔታ ባጣ ጊዜ በሕግ መሠረት ከምክር ቤት አባልነቱ ይወገዳል፤



www.abyssinialaw.com

መ) የዚህ አንቀጽ ንዑስ ፪/ሐ/ ድንጋጌ እንደ አግባብነቱ በየደረጃው በሚገኙ ምክር ቤቶች ተፈጻሚነት ይኖረዋል፤

ሠ) አንድ ሰው በአንድ ጊዜ የክልል ምክር ቤት እና የብሔረሰቦች ምክር ቤት ሊሆን አይችልም።

## ክፍል አንድ

## ስለክልሉ ምክር ቤት

### አንቀጽ ፶

### ስለ ክልሉ ምክር ቤት አባላት

፩· የክልሉ ምክር ቤት አባላት ነፃ፣ ቀጥተኛ፣ ትክክለኛ በሆነና ድምጽ በምሥጢር በሚሰጥበት ሥርዓት በየአምስት ዓመቱ በሕዝብ ይመረጣሉ።

፪· የምክር ቤት አባላት በአንድ የምርጫ ክልል ውስጥ ከሌሎች ተወዳዳሪዎች መካከል አብላጫ ድምጽ ያገኘ ተወዳዳሪ አሸናፊ በሚሆንበት የምርጫ ሥርዓት ይመረጣሉ። የተለየ ውክልና እንደሚያስፈልጋቸው የታመነባቸው ብሔረሰቦች ወይም ሕዝቦች በምርጫ ምክር ቤቱ ውስጥ ይወከላሉ። ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

፫· የምክር ቤቱ አባላት የመላው የክልሉ ሕዝብ ተወካዮች ናቸው። ተገዥነታቸውም፡-

ሀ) ለሕገ መንግሥቱ፤

ለ) ለሕዝብና፤ እና

ሐ) ለራሳቸው ሕሊና ብቻ ይሆናል።

### አንቀጽ ፶፩

### የክልሉ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

፩· የክልሉ ምክር ቤት በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት የክልሉ ሕግ

አውጭ አካል ነው።

፪· የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሕገ መንግሥት ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ በክልሉ የውስጥ ጉዳዮች ላይ የበላይ የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤት ነው።

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፪ ድንጋጌዎች ሥር የሰፈረው አጠቃላይ ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ በተለይ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፦

ሀ) በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት የፌዴራሉን ሕገ መንግሥትና ሌሎች ሕጎችን የማይፃረሩ ልዩ ልዩ ሕጎችን ያወጣል፤

ለ) የሕዝቡን ብዛት ፣ የአካባቢውን ስፋትና ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ግምት ውስጥ በማስገባት በክልሉ ውስጥ ተጨማሪ የአስተዳደር እርከኖችን ወይም የራስ በራስ አስተዳደራዊ አካባቢዎችን ያቋቁማል፤

ሐ) የፌዴራል መንግሥት ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ከአጎራባች ክልል መንግሥታት ጋር የሚደረገውን ስምምነት ያፀድቃል፤

መ) ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ርዕሰ መስተዳድሩን ይመርጣል። በርዕሰ መስተዳድሩ አቅራቢነት የክልል መስተዳድር ምክር ቤት አባላት ሹመት ያፀድቃል፤

ሠ) የኦዲትና የቁጥጥር አካሉን ያቋቁማል፤

ረ) በሕግ መሠረት ምሕረት ያደርጋል፤

ሰ) የክልሉን ሰላምና ፀጥታ ለመጠበቅ የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ያወጣል፤ የፀጥታና የፖሊስ ኃይሉን ያቋቁማል፤

ሸ) የክልሉን የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፕሮግራሞች ያጸድቃል፤

ቀ) የክልሉን የገቢ ምንጮች የሚመለከቱ ሕጎችን ያወጣል፤ የክልሉን መንግሥት በጀት ያጸድቃል፤

በ) ለማኅበራዊ አገልግሎት መስፋፋትና ለኢኮኖሚያዊ ልማት መፋጠን አስፈላጊ የሆኑ ተቋማትን ያቋቁማል፤



www.abyssinialaw.com

ተ) የክልሉን ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንት፣ ዋና ኦዲተሩንና ምክትል ዋና ኦዲተሩን ይሾማል፤

ቸ) ለክልሉ መንግሥት በተከለለው የገቢ ምንጭ በክልሉ ውስጥ ግብርና ታክስ ይጥላል፤

ኀ) የክልሉን የሠራተኛ አስተዳደርና የሥራ ሁኔታዎችን በተመለከተ ሕግ ያወጣል፤

ነ) የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያጸድቃል፤

ኘ) የክልሉን ርዕሰ መስተዳድርና ሌሎች የክልሉን መንግሥት ባለሥልጣናት ለጥያቄ ይጠራል። የአስፈጻሚውን አካል አሠራር ይመረምራል።

## አንቀጽ ፶፪

## የፖለቲካ ሥልጣን

፩· በምክር ቤቱ አብላጫ መቀመጫ ያገኘ የፖለቲካ ድርጅት ወይም ጣምራ የፖለቲካ ድርጅቶች የክልሉን መስተዳድር ምክር ያደራጃል ወይም ያደራጃሉ፣ ይመራል ወይም ይመራሉ።

፪· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እንደየአግባብነቱ ለዞን፣ለልዩ ወረዳ፣ ለወረዳና ለቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት ተፈጻሚ ይሆናል።

## አንቀጽ ፶፫

## የአፈጉባዔው ሥልጣንና ተግባር

፩· የምክር ቤቱን መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች ይጠራል፣ ይመራል ።

፪· ምክር ቤቱን በመወከል፣ ጠቅላላ የአስተዳደር ሥራዎችን የመራል።

፫· ምክር ቤቱ በአባሎቹ ላይ የወሰነውን የዲሲፕሊን እርምጃ ያስፈጽማል።

፬· የምክር ቤቱን ጽሕፈት ቤት አደረጃጀት በሕግ ይወስናል።

www.abyssinialaw.com

፫· የምክር ቤቱን ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎችን ያስተባብራል።

፬· በሕግ የተሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## አንቀጽ ፶፬

## የምክትል አፈጉባዔው ሥልጣንና ተግባር

፩· ምክትል አፈጉባዔ በአፈጉባዔው ተለይተው የተሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።

፪· አፈጉባዔው በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል።

## አንቀጽ ፶፭

## የምክር ቤቱ የስብሰባ ጊዜና የሥራ ዘመን

፩· ከምክር ቤቱ አባላት ውስጥ ከሁለት ሦስተኛ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።

፪· የክልል ምክር ቤት አባላት የሚመረጡት ለ፭ ዓመታት ነው ። የሥራ ዘመኑ ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሄዶ ይጠናቀቃል፣ የቀድሞው ምክር ቤት የሥራ ዘመን በተጠናቀቀ በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ አዲሱ ምክር ቤት ሥራውን ይጀምራል።

፫· ምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በማያደርግበት ወቅት አፈ ጉባዔው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል። ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከአንድ ሦስተኛ በላይ የሆኑት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ከጠየቁ አፈ ጉባዔው ምክር ቤቱን ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት።

፬· የክልሉ ምክር ቤት ስብሰባ በግልጽ ይካሄዳል፣ ሆኖም ስብሰባው በዝግ እንዲካሄድ በምክር ቤቱ አባላት ወይም በክልሉ አስፈጻሚ አካል ከተጠየቀና ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ጥያቄውን ከደገፉ ምክር ቤቱ ዝግ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።

## አንቀጽ ፶፮

## የምክር ቤቱ ውሳኔዎችና ውስጣዊ የአሠራር ሥነ ሥርዓቶች

፩· በዚህ ሕገ መንግሥት ውስጥ ተገልጾ በተለይ ካልተደነገገ በስተቀር ማናቸውም ውሳኔዎች የሚተላለፉት በስብሰባው ላይ ከተገኙት ምክር ቤት አባላት የአብላጫ ድምጽ ይሆናል።

፪· ምክር ቤቱ ውስጣዊ አሠራሩንና የሕግ አወጣጡን ሂደት አስመልክቶ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።

## አንቀጽ ፶፯

## ስለ ምክር ቤቱ መበተን

፩· ርዕሰ መስተዳድሩ የምክር ቤቱ የሥልጣን ዘመን ከማለቁ በፊት አዲስ ምርጫ ለማካሄድ በምክር ቤቱ ፈቃድ እንዲበተን ለማድረግ ይችላል።

፪· በጣምራ የክልሉን መንግሥት ሥልጣን የያዙ የፖለቲካ ድርጅቶች ጣምራነታቸው ፈርሶ በምክር ቤቱ የነበራቸውን አብላጫነት ያጡ እንደሆን የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ተበትኖ በክልሉ ምክር ቤት ባሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ሌላ ጣምራ መንግሥት በሁለት ሳምንት ጊዜ ውስጥ ለመመሥረት ርዕሰ መስተዳድሩ የፖለቲካ ድርጅቶችን ይጋብዛል። የፖለቲካ ድርጅቶቹ አዲስ መንግሥት ለመመሥረት ወይም የነበረውን ጣምራነት ለመቀጠል ካልቻሉ የክልሉ ምክር ቤት ተበትኖ አዲስ ምርጫ ይደረጋል።

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ ፩ ወይም ፪ መሠረት ምክር ቤቱ የተበተነ እንደሆነ ከስድስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ አዲስ ምርጫ መደረግ አለበት።

፬· ምርጫው በተጠናቀቀ በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ አዲሱ የክልል ምክር ቤት ሥራውን ይጀምራል።

፭· የክልሉ ምክር ቤት ከተበተነ በኋላ ክልሉን የሚመራው ሥልጣን ይዞ የነበረው የፖለቲካ ድርጅት ወይም የፖለቲካ ድርጅቶች ጣምራ የዕለት ተዕለት የመንግሥት ሥራ ከማከናወንና ምርጫ ከማካሄድ በስተቀር አዲስ አዋጆችን፣ ደንቦችንና ድንጋጌዎችን ከማውጣት ወይም ነባር ሕጎችን መሻርና ማሻሻል አይችልም።

፮· የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደየአግባብነቱ ዞን፣ ልዩ ወረዳ፣ በወረዳ እና በቀበሌ ምክር ቤቶች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

## ክፍል ሁለት

## የብሔረሰቦች ምክር ቤት

### አንቀጽ ፶፰

### የብሔረሰቦች ምክር ቤት አባላት

፩· የብሔረሰቦች ምክር ቤት በክልሉ የሚገኙት ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቢያንስ በአንድ አባል የሚወከሉበት ምክር ቤት ነው።

፪· እያንዳንዱ ብሔር፣ ብሔረሰብና ሕዝብ አንድ ሚሊዮን ሕዝብ አንድ ተጨማሪ አባል ይወከላል።

፫· የብሔረሰቦች ምክር ቤት አባላት ለዞን፣ ለልዩ ወረዳ ምክር ቤት ከተመረጡት አባላት መካከል ይወከላሉ። በዞን ምክር ቤት ውክልና ያላገኙ ብሔረሰቦች ለወረዳ ምክር ቤት ከተመረጡት አባላት ይወከላሉ። ውክልናቸውም በሚመለከተው ምክር ቤት የጸደቀ መሆን ይኖርበታል።



www.abyssinialaw.com

### አንቀጽ ፶፱

### የብሔረሰቦች ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

፩· ምክር ቤቱ የክልሉን ሕገ መንግሥት የመተርጎም ሥልጣን ይኖረዋል።

፪· የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔን ያደራጃል።

፫· የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የዞን፣ የልዩ ወረዳ፣ እና ወረዳ አስተዳደር መብት በተመለከተ በሚነሱ ጥያቄዎች ላይ በሕገ መንግሥቱ መሠረት ይወስናል።

፬· የክልሉ ሕዝቦች በእኩልነትና በመፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ አንድነት እንዲጠናከር እንዲጐለብት ያደርጋል።

፭· በክልሉ ውስጥ በሚገኙ አስተዳደር እርከኖች መካከል በሚነሱ አለመግባባቶች መፍትሄ ይፈልጋል። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

፮· የብሔረሰቦች ታሪክ፣ ባህል፣ ቋንቋ የሚጠናበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

፯· የክልሉ ሕገ መንግሥት ማሻሻያ ሀሳብ የማመንጨትና በማሻሻል ሂደት ውስጥ ይሣተፋል።

፰· ከአጐራባች ክልል መንግሥታት ጋር በሚነሱ አለመግባባቶችንና የድንበር መካለል ጥያቄዎችን አጥንቶ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ያቀርባል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል።

### አንቀጽ ፷

### የውሣኔዎችና የሥነ ሥርዓት ደንቦች

፩· ከአባላቱ ሁለት ሦስተኛው የተገኙ እንደሆነ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል። ማንኛውም የምክር ቤቱ ውሳኔ ስብሰባ ላይ በተገኙት

www.abyssinialaw.com

አባላት አብላጫ ድምጽ ይተላለፋል።

፪· አባላት ድምጽ መስጠት የሚችሉት በአካል ሲገኙ ብቻ ነው።

፫· ምክር ቤቱ ስለውስጣዊ አሠራሩና የስብሰባ አመራር ሥነ ሥርዓት ደንቦች ሊያወጣ ይችላል።

## አንቀጽ ፷፩
## በጀት

የብሔረሰቦች ምክር ቤት በጀቱን ለክልሉ ምክር ቤት አቅርቦ ያስወስናል።

## አንቀጽ ፷፪

የብሔረሰቦች ምክር ቤት አፈ ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር

አፈ ጉባዔው፦

፩· የምክር ቤቱን መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች ይጠራል፣ ይመራል።

፪· ምክር ቤቱን ይወክላል፣ ጠቅላላ የአስተዳደር ሥራዎችን ይመራል።

፫· ምክር ቤቱ በአባሎቹ ላይ የወሰደውን የዲስፒሊን እርምጃ ያስፈጽማል።

፬· የምክር ቤቱን ጽሕፈት ቤት ያደራጃል።

፭· የምክር ቤቱ ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎችን ያስተባብራል።

፮· በምክር ቤቱና በሕግ የተሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## አንቀጽ ፷፫
## የምክትል አፈ ጉባዔው ሥልጣንና ተግባር

፩· አፈ ጉባዔው በማይኖርበት ወይም ሥራውን ማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል።

፪· በአፈ ጉባዔው ተለይተው የተሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።



## ምዕራፍ ስድስት
## የክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት

## አንቀጽ ፷፬
## የአስፈጻሚነት ሥልጣን

፩·የክልሉ መንግሥት ከፍተኛ የአስፈጻሚነት ሥልጣን የተሰጠው ለርዕሰ መስተዳድሩና ለክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት ነው።

፪· ርዕሰ መስተዳድሩና የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ተጠሪነታቸው ለክልሉ ምክር ቤት ነው።

፫· የመስተዳድር ምክር ቤት አባላት በመንግሥት ተግባራቸው በጋራ ለሚሰጡት ውሳኔ የጋራ ኃላፊነት አለባቸው።

፬· "መስተዳድር" ማለት የክልሉ መንግሥት የሕግ አስፈጻሚው አካል ነው"

## አንቀጽ ፷፭
## የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት

፩· የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ርዕሰ መስተዳድሩ ፣ ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩና የአስፈጻሚ መሥሪያ ቤቶች ኃላፊዎች በአባልነት የሚገኙበት አካል ነው ። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል ።

፪· የክልል መስተዳድር ምክር ቤት ሰብሳቢ ርዕሰ መስተዳድሩ ነው ።

፫· የክልል መስተዳድር ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለርዕሰ መስተዳድሩ ነው።

፬· የክልል መስተዳድር ምክር ቤት በሚወስነው ውሳኔ ለክልሉ ምክር ቤት ተጠሪ ይሆናል ።

## አንቀጽ ፷፮
## የክልል መስተዳድር ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

የፌዴራል ሕገ መንግሥት ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልል መስተ

ዳድር ምክር ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል ።

፩· በክልሉ ምክር ቤትና በፌዴራሉ መንግሥት የወጡ ሕጎችና የተሰጡ ውሳኔዎች በክልሉ ውስጥ በሥራ መተርጎማቸውን ያረጋግጣል ፤ መመሪያዎችን ያወጣል።

፪· በሕግ በሚወሰነው መሠረት የክልሉን መስተዳድር ምክር ቤት ፤ ሌሎች አስፈጻሚ አካላትና ልዩ ልዩ ተቋማትን ያደራጃል ፤ ይቆጣጠራል ፤ ይመራል።

፫· የክልሉን መንግሥት በጀት ያዘጋጃል ፤ ለክልሉ ምክር ቤት ያቀርባል፤
ሲፀድቅም በተግባር ላይ እንዲውል ያደርጋል።

፬· የክልሉን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ይነድፋል ፤ የሕግ ረቂቆችን ለክልሉ ምክር ቤት አቅርቦ ያስፀድቃል ፤ የተወሰነውንም ያስፈጽማል።

፭· በክልሉ ውስጥ ሕግና ሥርዓት መከበሩን ያረጋግጣል ።

፮· የክልል ምክር ቤት በሚሰጠው ሥልጣን መሠረት ደንቦችን ያወጣል።

፯· የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያውጃል።

፰· በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፷፰ ንዑስ አንቀጽ ፪ (ሰ) መሠረት የሚቀርቡለትን ኃላፊዎች ይሾማል።

፱· የክልሉ ቅርሳ ቅርስና የተፈጥሮ ሀብት አስፈላጊው እንክብካቤና ጥበቃ የተደረገለት መሆኑን ያረጋግጣል።

፲· በክልሉ ምክር ቤትና በሕግ መሠረት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል ።

## አንቀጽ ፷፯
## የርዕሰ መስተዳድሩ አሰያየምና የሥራ ዘመን

፩· ርዕሰ መስተዳድሩ በክልሉ ምክር ቤት አብላጫ ድምፅ ባገኘው የፖለቲካ ድርጅት ወይም የፖለቲካ ድርጅቶች አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት በምርጫ ይሰየማል።



www.abyssinialaw.com

፪· በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር የርዕሰ መስተዳድሩ የሥራ ዘመን የክልል ምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ነው ።

## አንቀጽ ፷፰
## የርዕሰ መስተዳድሩ ሥልጣንና ተግባር

፩· ርዕሰ መስተዳድሩ የክልል መስተዳድር ሥራ መሪ ፤ የመስተዳድር ምክር ቤቱ ሰብሳቢና የክልሉ ፕሬዚዳንት ነው ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ርዕሰ መስተዳድሩ ፦

ሀ) የክልሉ መንግሥት ምክር ቤት ይመራል ፤ ያስተባብራል ፤ ይወክላል ፤

ለ) የክልሉን መንግሥት ምክር ቤትና መስተዳድር ምክር ቤት እንዲሁም የዞን፣ የልዩ ወረዳ ምክር ቤቶች በየበኩላቸው መክረው ያፀደቋቸውን አዋጆችና ደንቦች በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ ይፈርማል ፤ በደቡብ ነጋሪት ጋዜጣ ያውጃል ። ርዕሰ መስተዳድሩ በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ ካልፈረመ ሕጉ በሥራ ላይ ይውላል ፤

ሐ) የክልሉ መስተዳድርና ምክር ቤት ያወጣቸውን ፖሊሲዎች ፤ ደንቦች ፤ መመሪያዎችና ውሳኔዎች ተፈፃሚነት ይከታተላል ፤

መ) የክልሉን ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ፤ ምክትል ፕሬዚዳንት ፤ የክልሉን ዋና ኦዲተር ፤ ምክትል ዋና ኦዲተር ፤ ሹመት ለክልሉ ምክር ቤት በማቅረብ ያስጸድቃል ፤

ሠ) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪/መ/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ምክር ቤት ሊሰበሰብ ባልቻለበት ጊዜና ሁኔታ ከፍ ብሎ የተጠቀሱትን የሥራ ኃላፊዎች በጊዜያዊነት መድቦ ያሠራል ። የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት በጊዜያዊነት የሚመደቡት ከጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች መካከል ይሆናል ፤

ረ) የመስተዳድር ምክር ቤት አባላትን ለክልሉ ምክር ቤት በማቅረብ ሹመታቸውን ያስፀድቃል ። ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ የክልሉ ምክር ቤት አባል መሆን አለበት ፤

ሰ) የክልሉን ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና አስተዳደራዊ ተቋማትና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ (መ) እና (ረ) ሥር ከተዘረዘሩት ውጭ የሆኑ የክልል አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች ኃላፊዎችና ምክትል ኃላፊዎች በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በማቅረብ ያሾማል ፤

ሸ) የክልሉን ደህንነት ለመጠበቅና ሕግና ሥርዓትን ለማስከበር የተቋቋሙትን ክልል አቀፍ የፀጥታና የፖሊስ ኃይሎች በበላይነት ይመራል ፤ ይቆጣጠራል ፤

ቀ) በክልሉ የሚገኙትን የበታች የመስተዳድር እርከኖች ሥራ ይመራል ፤ ያስተባብራል ፤ ይቆጣጠራል ፤

በ የዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፷፯ ንዑስ አንቀጽ ፪ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ርዕሰ መስተዳድሩ የክልሉን ምክር ቤት መሥራች ጉባዔ ይጠራል ። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል ፤

ተ) በሕግ የተሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል ።

## አንቀጽ ፷፱

## የምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ ሥልጣንና ተግባር

ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ ተጠሪነቱ ለርዕሰ መስተዳድሩና ለመስተዳድር ምክር ቤት ሆኖ ፡–

ሀ( በርዕሰ መስተዳድሩ ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል ፤

ለ) ርዕሰ መስተዳድሩ በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል ።



www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ ፸

## የርዕሰ መስተዳድሩ ጽሕፈት ቤት

፩ ርዕሰ መስተዳድሩ የራሱ ጽሕፈት ቤት ይኖረዋል ።

፪· የርዕሰ መስተዳድሩ ጽሕፈት ቤት የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት በመሆን ጭምር ያገለግላል ።

፫· ጽሕፈት ቤቱ በርዕሰ መስተዳድሩ አቅራቢነት በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚሾም አንድ ልዩ ፀሐፊ ይመራል ።

፬· ልዩ ፀሐፊው ተጠሪነቱ ለርዕሰ መስተዳድሩ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል ፡–

ሀ) ጽሕፈት ቤቱን በሰው ኃይልና በቁሳቁስ ያደራጃል ፤

ለ) የመስተዳድሩን ሠነዶች በአግባቡ ይይዛል ፤ ይጠብቃል ፤

ሐ) የመስተዳድር ምክር ቤቱ ቃለ ጉባዔ በሚገባ መያዙን ያረጋግጣል ፤

መ) በርዕሰ መስተዳድሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## አንቀጽ ፸፩

ስለ ኢኮኖሚያዊ ፤ ማህበራዊና አስተዳደራዊ ተቋማት መቋቋም

የክልሉን ኢኮኖሚያዊ ፤ ማህበራዊና አስተዳደራዊ ሥራዎች የሚከናወኑ፣ የሚያስተባብሩና የሚመሩ ልዩ ልዩ ቢሮዎች ፤

ኮሚሽኖችና ሌሎች መሥሪያ ቤቶች እንደ አስፈላጊነታቸው በሕግ ይቋቋማሉ ።

## ምዕራፍ ሰባት

## ስለ ፍርድ ቤቶች አወቃቀርና የዳኝነት ሥልጣን

## አንቀጽ ፸፪

## ስለነፃ የዳኝነት አካል መቋቋም

፩· የክልሉ ነፃ የዳኝነት አካል በዚህ ሕገ መንግሥት ተቋቁሟል ።

፪· የዳኝነት ሥልጣን ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ወይም በሕግ የመዳኘነት ሥልጣን ከተሰጠው ተቋም ውጭ የሚያደርግና በሕግ የተደነገገውን የዳኝነት ሥርዓት የማይከተል ልዩ ወይም ጊዜያዊ ፍርድ ቤት አይቋቋምም።

## አንቀጽ ፸፫
## ስለ ባህለዊና ሐይማኖታዊ የዳኝነት አካላት

የዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፴፬ ንዑስ አንቀጽ ፭ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ ሕገ መንግሥት ከመጽደቁ በፊት በመንግሥት እውቅና አግኝተው ሲሰራባቸው የነበሩ ሐይማኖታዊና ባህላዊ የዳኝነት አካላት በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት እውቅና አግኝተው ይደራጃሉ።

## አንቀጽ ፸፬
## የዳኝነት ሥልጣን

፩· የክልሉ የዳኝነት ሥልጣን የፍርድ ቤቶች ብቻ ነው ።
፪· በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ የዳኝነት አካል ከማናቸውም የመንግሥት አካል ፣ ባለሥልጣን ወይም ሌላ ተፅዕኖ ነፃ ነው ።
፫· ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸውን በሙሉ ነፃነት ያከናውናሉ ። ከሕግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ አይመሩም ።
፬· ማንኛውም ዳኛ ከዚህ በታች በተጠቀሱት ሁኔታዎች ካልሆን በስተቀር በሕግ የተወሰነው የጡረታ ዕድሜ ከመድረሱ በፊት ከፍቃዱ ውጭ ከዳኝነት ሥራው አይነሳም ፡—
  ሀ) የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ በዳኞች የዲሲፕሊን ሕግ መሠረት ጥፋት ፈጽሟል ወይም ጉልህ የሥራ ችሎታና ቅልጥፍና አንሶታል ብሎ ሲወስን ፤ ወይም
  ለ) በሕመም ምክንያት ዳኛው ተግባሩን በተገቢው ሁኔታ ማከናወን አይችልም ብሎ ሲወስን ፤ እና
  ሐ) የጉባዔው ውሳኔ ለክልሉ ምክር ቤት ቀርቦ በአባላቱ የአብላጫ ድምፅ ሲደግፍና ሲፀድቅ ።
፭· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ መሠረት አንድ ዳኛ ከዳኝነት ሥራው የሚያስነሳ ጥፋት ፈጽሟል ብሎ ጉባዔው ከወሰነበት ጉዳዩ ለክልሉ



www.abyssinialaw.com

ምክር ቤት ቀርቦ እስኪታይ ድረስ ከዳኝነት ሥራው ታግዶ መቆየት ይኖርበታል ።
፯· የማንኛውም ዳኛ የጡረታ መውጫ ጊዜ አይራዘምም ።

## አንቀጽ ፸፭
## የፍርድ ቤቶች አደረጃጀትና ሥልጣን

፩· የክልሉ የዳኝነት አካል በጠቅላይ ፍርድ ቤት ፣ በከፍተኛ ፍርድ ቤቶችና በወረዳ ፍርድ ቤቶች ይደራጃል ። የወረዳ ፍርድ ቤት የክልሉ የበታችና የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት አካል ነው ።
፪· የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፡—
  ሀ) ክልላዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ከፍተኛውና የመጨረሻው የዳኝነት ሥልጣን ፤
  ለ) በፌዴራል ጉዳዮች ላይ የፌዴራሉ መንግሥት ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን ፤ እና
  ሐ) ማናቸውም ክልላዊ ፍርድ ቤት በክልላዊ ጉዳዮች ላይ የሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ሲኖርበት በሰበር ችሎት የማየት ሥልጣን ይኖረዋል ። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።
፫· የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ካለው ክልላዊ ሥልጣን በተጨማሪ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል ።
፬· የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣኑ መሠረት በሚሰጠው ውሳኔ ላይ የሚቀርበው ይግባኝ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይታያል ።
፭· የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባለው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣኑ መሠረት በሚሰጠው ውሳኔ ላይ የሚቀርበው ይግባኝ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይታያል ።
፮· የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የዳኝነት አካላቱን የሚያስተዳድርበትን በጀት የክልሉ ምክር ቤት ይመድባል ። ሲፈቀድም በጀቱን

ያስተዳድራል ።

፯· የክልሉ ፍርድ ቤቶች በውክልና የሚፈፀሙትን ፌዴራላዊ የዳኝነት ተግባር ለማከናወን የሚወጡትን የገንዘብ ወጪ በተመለከተ ከፌዴራል መንግሥት ማካካሻ እንዲሰጣቸው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጥያቄ ያቀርባል።

## አንቀጽ ፸፮
## የዳኞች አሿሿም

፩· የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማሉ።

፪· የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤቶች እና የወረዳ ፍርድ ቤቶች ዳኞች በክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማሉ ።

፫· የክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ የክልሉን ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤቶች እና የወረዳ ፍርድ ቤቶች ዳኞች ሹመት በክልሉ ምክር ቤት ከማቅረቡ በፊት፣ የፌዴራሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ዕጩ ዳኞች እንዲሁም የሆኑ ወይም የልዩ ወረዳው አስተዳደር ምክር ቤት በከፍተኛና በወረዳ ፍርድ ቤቶች ዕጩ ዳኞች ላይ ያላቸውን አስተያየት መጠየቅና የተሰጠውን አስተያየት ከራሱ መግለጫ ጋር ለክልሉ ምክር ቤት የማቅረብ ኃላፊነት አለበት ። ሆኖም የፌዴራሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ የተጠየቀውን አስተያየት በሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ ካላቀረበ የክልሉ ምክር ቤት የዕጩ ዳኞቹን ሹመት ያፀድቃል ።

፬· በየትኛውም ደረጃ የሚገኙ ዳኞች የዲስፕሊንና የዝውውር ጉዳይ በክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ይወሰናል ።



www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ ፸፯
## የክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ መቋቋም

፩· በክልሉ ውስጥ ዳኞች በአብላጫ ድምፅ የሚወከሉበት የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ይቋቋማል ።

፪· የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ጉባዔውን ይሰበስባል ፣ ይመራል ።

፫· የጉባዔው አባላት ዝርዝር ፣ ጥንቅር ፣ ሥልጣንና ተግባር በሕግ ይወሰናል ።

## አንቀጽ ፸፰
## የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ

፩· የክልሉ ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ በዚህ ሕገ መንግሥት ተቋቁሟል ።

፪· የክልሉ ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ አሥራ አንድ አባላት የሚኖሩት ሲሆን እነርሱም የሚከተሉት ናቸው፡–

ሀ) የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ሰብሳቢ ፣

ለ) የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት ምክትል ሰብሳቢ ፣

ሐ) በርዕሰ መስተዳድሩ አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት የሚሰየሙ በሙያ ብቃታቸውና በሥነ ምግባራቸው የተመሰከረላቸው ስድስት የሕግ ባለሙያዎች ፣

መ) በአፈ ጉባዔው አቅራቢነት ከብሔረሰቦች ምክር ቤት አባላት መካከል በምርጫ የሚሰየሙ ሦስት ተወካዮች ።

## አንቀጽ ፸፱
## የአጣሪ ጉባዔው ሥልጣንና ተግባር

፩· የክልሉ ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ከክልሉ የሚመነጩ ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮችን የማጣራት ሥልጣን ይኖረዋል ። በሚያደርገው ማጣራት መሠረት የክልሉን ሕገ መንግሥት

መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በጉዳዩ ላይ የራሱን የውሳኔ ሃሳብ አዘጋጅቶ ለብሔረሰቦች ምክር ቤት ያቀርባል ።

፪· ጉባዔው በክልሉ መንግሥት አካላት የወጡ ሕጎች ፣ ከዚህ ሕገ መንግሥት ጋር ይቃረናሉ የሚል ጥያቄ በማናቸውም ሁኔታ ሲነሳና ጉዳዩ በሚመለከተው ፍርድ ቤት ወይም በባለጉዳዮች አማካኝነት ሲቀርብለት ከመረመረና ካጣራ በኋላ ለመጨረሻ ውሣኔ ለብሔረ ሰቦች ምክር ቤት ያቀርባል ።

፫· በፍርድ ቤቶች የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ሲነሳ ጉባዔው ፦

ሀ) የክልሉን ሕገ መንግሥት መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ ሳያገኘው ሲቀር ጉዳዩን ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ወዲያውኑ ይመልሳል ። ሆኖም በአጣሪ ጉባዔው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማናቸውም ባለጉዳይ ይህንኑ ቅሬታውን በጽሑፍ አዘጋጅቶ ለብሔረሰቦች ምክር ቤት በይግባኝ ማቅረብ ይችላል ፤

ለ) የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መኖሩን ያመነበት እንደሆነ በጉዳዩ ላይ የሚሰጠውን ሕገ መንግሥታዊ ትርጉም አሰናድቶ ለብሔረሰቦች ምክር ቤት ለመጨረሻ ውሣኔ ያቀርባል ።

## ምዕራፍ ስምንት

## የዞን ወይም የልዩ ወረዳ አደረጃጀትና ሥልጣን

### አንቀጽ ፹

### የዞን ወይም የልዩ ወረዳ አደረጃጀት

፩· ዞን ወይም ልዩ ወረዳ ከክልል ቀጥሎ የሚገኝ የአስተዳደር እርከን ነው ።

፪· እያንዳንዱ ዞን ወይም ልዩ ወረዳ የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል ፦

ሀ) የዞን ወይም የልዩ ወረዳ ምክር ቤት ፤

ለ) የዞን ወይም የልዩ ወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት ፤

ሐ) የዳኝነት አካል ።



www.abyssinialaw.com

### አንቀጽ ፹፩

### የዞን ወይም የልዩ ወረዳ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

፩· የዞን ወይም የልዩ ወረዳ ምክር ቤት ለክልል ምክር ቤት አባልነት የተመረጡትን ጨምሮ ከየወረዳው ለዞን ወይም ለልዩ ወረዳ ምክር ቤት የሚመረጡ አባላት ያሉበት ሆኖ ይቋቋማል ።

፪· በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ለፌዴራሉ የሕዝብ ተወካዮችና ለፌዴሬሽን ምክር ቤቶች በዚህ ሕገ መንግሥት ደግሞ ለክልሉ ምክር ቤት የተሰጣቸውን ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የዞን ወይም የልዩ ወረዳ ምክር ቤቶች በዞኑ ወይም በልዩ ወረዳው ውስጥ የበላይ የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤቶች ናቸው ።

፫· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ እያንዳንዱ የዞን ወይም ልዩ ወረዳ ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለመረጠው ሕዝብ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ) የሚጠቀምበትን የሥራ ቋንቋ ይወስናል ፤

ለ) ብሔረሰቡ በቋንቋው ለመናገርን ለመጻፍ ፣ ቋንቋውን ለማሳደግ፣ እንዲሁም ታሪኩን ለመንከባከብ ያለውን መብት ያስጠብቃል ፤

ሐ) በዚህ ሕገ መንግሥት ለክልሉ ምክር ቤት የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ በፌዴራልና በክልል በወጡ ሕጎች ባልተ ሸፈኑ ጉዳዮች ላይ እንዚህን ሕጐች በማይፃረር ሁኔታ ሕጐች ፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ያወጣል ። የምክር ቤቱ አፈ ጉባዔ ፈርሞ የላከውን ርዕሰ መስተዳድሩ በደቡብ ነጋሪት ጋዜጣ ያውጃል ፤

መ) የክልሉ ምክር ቤት ያፀደቀውን ዕቅድና በጀት መሠረት በማድረግ የዞኑን ወይም ልዩ ወረዳውን ዕቅድና በጀት መርምሮ ያፀድቃል ፤

ሠ) ከዞኑ ወይም ከልዩ ወረዳው ምክር ቤት አባላት መካከል አፈ ጉባዔውን ፣ ምክትል አፈ ጉባዔውንና ዋና አስተዳዳሪውን መርጦ ይሰይማል ፤

www.abyssinialaw.com

ረ) በዋና አስተዳዳሪው የሚቀርቡለትን የዞን ወይም ልዩ ወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት ሹመት መርምሮ ያፀድቃል ፤

ሰ) የከፍተኛና የወረዳ ፍርድ ቤቶች ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት ከየፍርድ ቤቱ ዳኞች መካከል በዋና አስተዳዳሪው አቅራቢነት ይሰየማል ፤

ሸ) የዞኑን ወይም የልዩ ወረዳውን ዋና አስተዳዳሪ፣ ሌሎች ባለሥልጣናት ለጥያቄ ይጠራል፣ አሠራራቸውን ይመረምራል።

## አንቀጽ ፳፪

## የዞን ወይም ልዩ ወረዳ ምክር ቤት አመራር

፩· የዞን ወይም ልዩ ወረዳ ምክር ቤት በምክር ቤቱ አብላጫ ድምጽ ባገኘው የፖለቲካ ድርጅት ወይም የፖለቲካ ድርጅቶች አቅራቢነት በሚመረጥ አፈ ጉባዔና ምክትል አፈ ጉባዔ ይመራል ።

፪· የአፈ ጉባዔውንና ምክትል አፈ ጉባዔውን ሥልጣንና ተግባር አስመልክቶ በዚህ ሕገ መንግሥት ለክልሉ ምክር ቤት አፈ ጉባዔና ምክትል አፈ ጉባዔ የተዘረጉት ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው ለዞንና ለልዩ ወረዳ ምክር ቤቶች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል ።

፫· ምክር ቤቱ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ንዑሳን ኮሚቴዎች ያደራጃል ።

## አንቀጽ ፳፫

## የዞን ወይም የልዩ ወረዳ ምክር ቤት የሥራ ዘመንና የስብሰባ ጊዜ

፩· የዞን ወይም የልዩ ወረዳ ምክር ቤት የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል ። የሥራ ዘመኑ ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሄዶ ይጠናቀቃል ። የቀድሞው ምክር ቤት የሥራ ዘመኑ በተጠናቀቀ በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ አዲሱ ምክር ቤት ሥራውን ይጀምራል ።

፪· የዞን ወይም የልዩ ወረዳ ምክር ቤት ቢያንስ በዓመት ሦስት ጊዜ ይሰበሰባል።

፫· ከምክር ቤቱ አባላት ከሁለት ሦስተኛው በላይ ከተገኙ ምልአተ ጉባዔ ይሆናል ። የምክር ቤቱ ውሣኔ በስብሰባ ላይ ከተገኙት አባላት አብላጫ ድምጽ ይተላለፋል ።

፬· የምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በማይደረግበት ወቅት አፈ ጉባዔው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል ። ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከአንድ ሦስተኛ በላይ የሆኑት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ከጠየቁ አፈ ጉባዔው ምክር ቤቱን ለስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት ።

## አንቀጽ ፳፬

## የዞን ወይም የልዩ ወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት

፩· የዞን ወይም ልዩ ወረዳ ከፍተኛ የሕግ አስፈጻሚ አካል የዞን ወይም ልዩ ወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት ሲሆን ተጠሪነቱም ለሚመለከተው ዞን ወይም ልዩ ወረዳ ዋና አስተዳደር፣ ለዚሁ ዞን ወይም ልዩ ወረዳ ምክር ቤት እና ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይሆናል።

፪· የዞን ወይም የልዩ ወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት የዞኑ ወይም የልዩ ወረዳው ዋና አስተዳዳሪ ፣ ምክትል ዋና አስተዳዳሪና በዞኑ ወይም ልዩ ወረዳው ውስጥ የሚገኙ አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች ኃላፊዎች በአባልነት የሚገኙበት አካል ሆኖ ይቋቋማል ።

፫· የዞኑ ወይም የልዩ ወረዳው አስተዳደር ምክር ቤት አባላት በጋራ ለወሰኑት ውሣኔና በፈፀሙት ተግባር የጋራ ኃላፊነት አለባቸው።

## አንቀጽ ፳፭

## የዞን ወይም የልዩ ወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

የዞን ወይም የልዩ ወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

www.abyssinialaw.com

ረ) በዋና አስተዳዳሪው የሚቀርቡለትን የዞን ወይም ልዩ ወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት ሹመት መርምሮ ያፀድቃል ፤

ሰ) የከፍተኛና የወረዳ ፍርድ ቤቶች ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት ከየፍርድ ቤቱ ዳኞች መካከል በዋና አስተዳዳሪው አቅራቢነት ይሰየማል ፤

ሸ) የዞኑን ወይም የልዩ ወረዳውን ዋና አስተዳዳሪ፣ ሌሎች ባለሥልጣናት ለጥያቄ ይጠራል፣ አሠራራቸውን ይመረምራል።

## አንቀጽ ፹፪

## የዞን ወይም ልዩ ወረዳ ምክር ቤት አመራር

፩· የዞን ወይም ልዩ ወረዳ ምክር ቤት በምክር ቤቱ አብላጫ ድምጽ ባገኘው የፖለቲካ ድርጅት ወይም የፖለቲካ ድርጅቶች አቅራቢነት በሚመረጥ አፈ ጉባዔና ምክትል አፈ ጉባዔ ይመራል ።

፪· የአፈ ጉባዔውንና ምክትል አፈ ጉባዔውን ሥልጣንና ተግባር አስመልክቶ በዚህ ሕገ መንግሥት ለክልሉ ምክር ቤት አፈ ጉባዔና ምክትል አፈ ጉባዔ የተገፉት ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው ለዞንና ለልዩ ወረዳ ምክር ቤቶች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል ።

፫· ምክር ቤቱ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ንዑሳን ኮሚቴዎች ያደራጃል ።

## አንቀጽ ፹፫

## የዞን ወይም የልዩ ወረዳ ምክር ቤት
## የሥራ ዘመንና የስብሰባ ጊዜ

፩· የዞን ወይም የልዩ ወረዳ ምክር ቤት የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል ። የሥራ ዘመኑ ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሂዶ ይጠናቀቃል ። የቀድሞው ምክር ቤት የሥራ ዘመኑ በተጠናቀቀ በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ አዲሱ ምክር ቤት ሥራውን ይጀምራል ።

፪· የዞን ወይም የልዩ ወረዳ ምክር ቤት ቢያንስ በዓመት ሦስት ጊዜ ይሰበሰባል።

፫· ከምክር ቤቱ አባላት ከሁለት ሦስተኛው በላይ ከተገኙ ምልአተ ጉባዔ ይሆናል ። የምክር ቤቱ ውሳኔ በስብሰባ ላይ ከተገኙት አባላት አብላጫ ድምጽ ይተላለፋል ።

፬· የምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በማይደረግበት ወቅት አፈ ጉባዔው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል ። ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከአንድ ሦስተኛ በላይ የሆኑት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ከጠየቁ አፈ ጉባዔው ምክር ቤቱን ለስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት ።

## አንቀጽ ፹፬

## የዞን ወይም የልዩ ወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት

፩· የዞን ወይም ልዩ ወረዳ ከፍተኛ የሕግ አስፈፃሚ አካል የዞን ወይም ልዩ ወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት ሲሆን ተጠሪነቱም ለሚመለከተው ዞን ወይም ልዩ ወረዳ ዋና አስተዳደሪ፣ ለዚሁ ዞን ወይም ልዩ ወረዳ ምክር ቤት እና ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይሆናል።

፪· የዞን ወይም የልዩ ወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት የዞኑ ወይም የልዩ ወረዳው ዋና አስተዳዳሪ ፣ ምክትል ዋና አስተዳዳሪና በዞኑ ወይም ልዩ ወረዳው ውስጥ የሚገኙ አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች ኃላፊዎች በአባልነት የሚገኙበት አካል ሆኖ ይቋቋማል ።

፫· የዞኑ ወይም የልዩ ወረዳው አስተዳደር ምክር ቤት አባላት በጋራ ለወሰኑት ውሳኔና በፈፀሙት ተግባር የጋራ ኃላፊነት አለባቸው።

## አንቀጽ ፹፭
## የዞን ወይም የልዩ ወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት
## ሥልጣንና ተግባር

የዞን ወይም የልዩ ወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፱· በክልሉ ምክርቤትና በፌዴራሉ መንግሥት አካላት የወጡ ሕጎችና የተሰጡ ውሳኔዎች በዞኑ ወይም በልዩ ወረዳው ውስጥ በሥራ መተርጎማቸውን ያረጋግጣል፤

፲· የዞኑን ወይም የልዩ ወረዳውን ሌሎች አስፈፃሚ አካላት አደረጃጀት ይወስናል፤ ሥራቸውን ይከታተላል፤ ይመራል፤

፲፩· የዞኑን ወይም የልዩ ወረዳውን በጀት ረቂቅ ያዘጋጃል፤ ለዞን ወይም ለልዩ ወረዳ ምክር ቤት ያቀርባል፤ ሲፀድቅም በተግባር ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

፲፪· ክልላዊ የሆኑ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን ሳይቃረን የዞኑን ወይም የልዩ ወረዳውን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን ይነድፋል፤ በዞኑ ወይም በልዩ ወረዳው ምክር ቤት ያስፀድቃል፤ የተወሰነውንም ያስፈፅማል።

፲፫· በዞኑ ወይም በልዩ ወረዳው ውስጥ ሕግና ሥርዓት መከበሩን ያረጋግጣል ፤

፲፬· ከክልሉ ሕገ መንግሥትና ሌሎች ሕጎች ጋር የማይፃረሩ መመሪያ ዎችን ያወጣል ፤

፲፭· የዞኑን ወይም የልዩ ወረዳውን ቅርሳ ቅርስና የተፈጥሮ ሀብት አስፈላጊው እንክብካቤና ጥበቃ የተደረገለት መሆኑን ያረጋግጣል፤

፲፮· የዞን ወይም የልዩ ወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት በዳኞች ሹመት ላይ የበኩሉን አስተያየት ለክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ይሰጣል፤

፲፯· ከዞን ወይም ከልዩ ወረዳ ምክር ቤትና በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

<u>አንቀጽ ፹፯</u>

<u>የዞን ወይም የልዩ ወረዳ ዋና አስተዳዳሪ</u>

<u>አሰያየምና የሥራ ዘመን</u>

፩· ዋና አስተዳዳሪው በዞኑ ወይም በልዩ ወረዳው ምክር ቤት አብላጫ ድምጽ ባገኘው የፖለቲካ ድርጅት ወይም የፖለቲካ ድርጅቶች



www.abyssinialaw.com

አቅራቢነት በዞኑ ወይም በልዩ ወረዳው ምክር ቤት በምርጫ ይሰየማል።

፪· በዚህ ሕገመንግሥት በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር የዋና አስተዳዳሪው ሥራ ዘመን የምክር ቤቱ ሥራ ዘመን ነው ።

<u>አንቀጽ ፹፰</u>

<u>የዞኑ ወይም የልዩ ወረዳው ዋና አስተዳዳሪ</u>

<u>ሥልጣንና ተግባር</u>

፩· ዋና አስተዳዳሪው የዞኑ ወይም የልዩ ወረዳው አስተዳደር ሥራ መሪ፣ የአስተዳደሩ ምክር ቤት ሰብሳቢና አስተዳዳሪ ነው ።

፪· ዋና አስተዳዳሪው ለዞኑ ወይም ልዩ ወረዳው ምክር ቤትና ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ተጠሪ ሆኖ፦

ሀ) የዞኑ ወይም የልዩ ወረዳውን አስተዳደር ምክር ቤት ይመራል፤ ይወክላል፤

ለ) የፌዴራሉንና የክልሉን ሕግጋተ መንግሥታት ፤ ፖሊሲዎች ፤ ሕጎች ፤ ደንቦች ፤ መመሪያዎችና ፕሮግራሞች በዞኑ ወይም የልዩ ወረዳው ውስጥ በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል ፤

ሐ) የዞኑ ወይም የልዩ ወረዳው አስተዳደር ምክር ቤት አባላትን ለምክር ቤቱ አቅርቦ ያሾማል። ምክትል ዋና አስተዳዳሪው የምክር ቤት አባል መሆን አለበት፤

መ) የዞኑን ወይም ልዩ ወረዳውን ሰላምና ደህንነት ለመጠበቅ ፤ ሕግና ሥርዓትን ለማስከበር የቆሙትን የፀጥታና የፖሊስ ኃይሎች በበላይነት ይመራል ፤ ይቆጣጠራል ፤

ሠ) በዞኑ ወይም በልዩ ወረዳው የሚገኙትን የቢሮዎች አስተዳደር እርከኖችንና አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶችን ይመራል ፤ ይቆጣጠራል ፤

ረ) ለዞኑ ወይም ለልዩ ወረዳው ምክር ቤትና ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር በየጊዜው ሪፖርት ያቀርባል፤

ለ) በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፹፯ ንዑስ አንቀጽ ፪ ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና አስተዳዳሪው የዞኑ ወይም ልዩ ወረዳውን ምክር ቤት መሥራች ጉባዔ ይጠራል፤

ሐ) የዞኑን ወይም የልዩ ወረዳውን ከፍተኛና ወረዳ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ከፍርድ ቤቱ ዳኞች መካከል መርጦ በምክር ቤት ያስጸድቃል፤

ተ) በዞኑ ወይም በልዩ ወረዳው ምክር ቤትና በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር የተሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

አንቀጽ ፹፰

<u>የዞኑ ወይም የልዩ ወረዳው ምክትል ዋና አስተዳዳሪ</u>

<u>ሥልጣንና ተግባር</u>

ምክትል ዋና አስተዳዳሪው ተጠሪነቱ ለዋናው አስተዳዳሪና ለዞኑ ወይም ለልዩ ወረዳው አስተዳደር ምክር ቤት ሆኖ፦

ሀ) በዋናው አስተዳዳሪና በዞኑ ወይም በልዩወረዳው አስተዳደር ምክር ቤት ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤

ለ) ዋናው አስተዳዳሪ በማይኖርበት ወይም ሥራውን ማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል ።

<u>አንቀጽ ፹፱</u>

<u>የዞኑ ወይም የልዩ ወረዳው ዋና አስተዳዳሪ ጽሕፈት ቤት</u>

፩· የዞኑ ወይም የልዩ ወረዳው አስተዳደር ጽሕፈት ቤት በዋና አስተዳዳሪው ተመርጦ በሚመደብ አንድ የሥራ ኃላፊ ይመራል።

፪· ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ጽሕፈት ቤት የተደነገገው ድንጋጌ ለዞንና፣ ለልዩ ወረዳ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት እንደአግባብነቱ ተፈጻሚ ይሆናል።



www.abyssinialaw.com

<u>ምዕራፍ ዘጠኝ</u>

<u>የወረዳ አስተዳደር አደረጃጀትና ሥልጣን</u>

<u>አንቀጽ ፺</u>

<u>አደረጃጀት</u>

የወረዳ አስተዳደር ከዞን አስተዳደር በታች የሚደራጅ የመንግሥት አስተዳደር መዋቅር ሆኖ የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፦

፩· የወረዳ ምክር ቤት ፤

፪· የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት ፤

፫· የወረዳ የዳኝነት አካል ።

<u>አንቀጽ ፺፩</u>

<u>የወረዳ አስተዳደር ሥልጣንና ተግባር</u>

፩· የወረዳ አስተዳደር በተደራጀበት ክልል ውስጥ የኢኮኖሚያዊ ልማትና ማኅበራዊ አገልግሎት እቅዶችን ለማዘጋጀትና ለመወሰንም ሆነ የክልሉ መንግሥት አካላት በየጊዜው የሚያወጡዋቸውን ፖሊሲዎች ፡ ሕጎች ፡ ደንቦችና መመሪያዎች በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ማናቸውም ሥልጣን ይኖረዋል ።

፪· እያንዳንዱ ወረዳ አስተዳደር አካባቢውን የማልማትና በውስጣዊ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ የመስጠት መብትና ሥልጣኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልል መስተዳድሩ የተደራጀበት ዞን የበታች አካል ነው።

<u>አንቀጽ ፺፪</u>

<u>የወረዳ ምክር ቤት አባላት</u>

<u>አመራረጥና ተጠሪነት</u>

፩· የወረዳ ምክር ቤት አባላት ወረዳው የተደራጀበት አካባቢ

www.abyssinialaw.com

ከሚገኙት የቀበሌ ነዋሪዎች መካከል በቀጥታ በሕዝብ ይመረጣሉ ።

፪· የወረዳ ምክር ቤት አባላት ተጠሪነት ለመረጣቸው ሕዝብ ይሆናል።

## አንቀጽ ፶፫

## የወረዳ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

፩· የወረዳ ምክር ቤት በተቋቋመበት ወረዳ ውስጥ ከፍተኛው መንግሥታዊ የሥልጣን አካል ነው። ተጠሪነቱም ለመረጠው ሕዝብ ይሆናል።

፪· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ) የወረዳውን ኢኮኖሚያዊ ልማት፣ ማህበራዊ አገልግሎቶችና አስተዳደራዊ የሥራ እቅዶች፣ ፕሮግራሞችና በጀት ረቂቅ መርምሮ ያፀድቃል፤

ለ) በወረዳው ውስጥ መሠረታዊ የግብርና ልማት ሥራዎች ወቅቱን ጠብቀው መካሄዳቸውንና የተፈጥሮ ሃብት ልማት፣ ጥበቃና እንክብካቤ ሥራ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት መከናወኑን ይከታተላል፤

ሐ) ነዋሪውን ሕዝብ ለልማት ሥራ በስፋት የሚነሣሣበትንና የሚንቀሳቀስበትን አመች ሁኔታ ይፈጥራል፤

መ) ከምክር ቤቱ አባላት መካከል አፈ ጉባዔውንና ምክትል አፈ ጉባዔውን፣ ዋና አስተዳዳሪውን በምርጫ ይሰይማል፤ በዋና አስተዳዳሪው የሚቀርቡለትን የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት ሹመት ያፀድቃል፤

ሠ) የራሱን ውስጣዊ የአሠራር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ያወጣል፤

ረ) ዝርዝሩ በሕግ የሚወሰን ሆኖ የመሬት መጠቀሚያ ታክስን የእርሻ ሥራ ገቢ ግብርን፣ የግብርና ውጤቶች ሽያጭ ግብር፣ ሌሎች የአገልግሎት ታክሶችንና ክፍያዎችን መሰብሰባቸውን



ያረጋግጣል፤

ሰ) ክልሉ ከሚመድበውና ከሚያስተዳድረው ውጭ ያለውን የወረዳው የገቢ ምንጭ ይጠቀማል፤ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፤

ሸ) የፌዴራሉና የክልሉ ሕገ-መንግሥታትና ሌሎች ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው የወረዳውን ሠላምና ፀጥታ ለማረጋገጥ የሚያስችል መመሪያ አውጥቶ በሥራ ላይ ያውላል፤

ቀ) የወረዳውን ዋና አስተዳዳሪ፣ ሌሎች ባለሥልጣናት ለጥያቄ ይጠራል፤ አሠራራቸውንም ይመረምራል።

## አንቀጽ ፶፬

## የምክር ቤቱ አመራርና አፈጉባኤ

፩· የወረዳ ምክር ቤት አብላጫ ድምጽ ባገኘው የፖለቲካ ድርጅት ወይም የፖለቲካ ድርጅቶች አቅራቢነት ተመርጦ በሚሰየም አፈ ጉባዔ እና ምክትል አፈ ጉባኤ ይመራል።

፪· በዚህ ሕገመንግሥት ስለክልሉ ምክር ቤት አፈጉባዔ ሥልጣንና ተግባር አስመልክቶ የተደነገጉት ለወረዳ ምክርቤት አፈጉባዔ እንደአግባብነቱ ተፈፃሚ ይሆናል።

## አንቀጽ ፶፭

## የምክር ቤቱ ምክትል አፈ ጉባዔ

፩· ምክትል አፈ ጉባዔው፣ በአፈ ጉባዔው ተለይተው የተሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።

፪· አፈ ጉባዔው በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል።

## አንቀጽ ፶፮

## የምክር ቤቱ የስብሰባ ጊዜና የሥራ ዘመን

፩· የወረዳ ምክር ቤት በየሶስት ወሩ ይሰበሰባል።

www.abyssinialaw.com

፪· ከምክር ቤቱ አባላት ከሁለት ሶስተኛ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፤ የምክር ቤቱ ውሣኔ በስብሰባ ላይ ከተገኙት የምክር ቤቱ አባላት አብላጫ ድምፅ ይተላለፋል።

፫· የወረዳ ምክር ቤት የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል። የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ከማብቃቱ አንድ ወር በፊት አዲሱ ምርጫ ተካሂዶ ይጠናቀቃል። የቀድሞው ምክር ቤት ሥራ ዘመን በጠተናቀቀ በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ አዲስ ምክር ቤት ሥራውን ይጀምራል።

፬· የወረዳ ምክር ቤት ስብሰባ በግልፅ ይካሄዳል። ምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በሚያደርግበት ወቅት አፈጉባዔው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል። ከምክር ቤቱ አባላት መካከል አንድ ሦስተኛ የሚሆኑት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲካሄድ ከጠየቁ አፈጉባዔው የምክር ቤቱ አስቸኳይ ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት።

## አንቀጽ ፺፯
## የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት

፩· የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት የተቋቋመበት ወረዳ ከፍተኛ ሕግ አስፈፃሚ አካል ሲሆን ተጠሪነቱም ለዋና አስተዳዳሪውና ለወረዳው ምክር ቤት ነው።

፪· የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ ፣ ምክትል ዋና አስተዳዳሪ፣ እንዲሁም የወረዳው አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች ኃላፊዎች በአባልነት የሚገኙበት አካል ነው።

## አንቀጽ ፺፰
## የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

፩· የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

ሀ) የፌዴራሉና የክልሉ መንግሥታት ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ እቅዶችና ፕሮግራሞች በተቋቋመበት ወረዳ ውስጥ በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

ለ) በወረዳው ውስጥ የሚገኙ አስፈፃሚ አካላትና ጽህፈት ቤቶቻቸውን በበላይነት ያስተባብራል፤ ሥራቸውን ይከታተላል፤ ይመራል፤

ሐ) የወረዳውን በጀት ረቂቅ ያዘጋጃል፤ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፤ ሲፀድቅም በተግባር ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

መ) የወረዳውን ሠላምና ፀጥታ ይጠብቃል፤ የወረዳውን የፀጥታና የፖሊስ አካላት ይመራል፤ ሥራቸውን ያስተባብራል፤

ሠ) የማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊና አስተዳደራዊ እቅዶችን አዘጋጅቶ ለወረዳው ምክር ቤት በማቅረብ ያስጸድቃል ።

ረ) የተፈጥሮ ሃብትን ይጠብቃል፤ ያለማል፤ ይንከባከባል፤ ሕዝቡን ለልማት ሥራ በስፋት ያንቀሳቅሳል፤

ሰ) በወረዳው ውስጥ የሚገኝ ማናቸውም ቅርሣ ቅርስ አስፈላጊው ጥበቃና እንክብካቤ የተደረገለት ስለመሆኑ በቅርበት ይከታተላል፤

ሸ) በወረዳው ምክር ቤትና በዞን አስተዳደር ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

፪· የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት በመንግሥታዊ ሥልጣናቸው ለሚፈጽሙት ተግባርና ለሚያሳልፉት ውሳኔ በጋራ ኃላፊነት አለባቸው።

## አንቀጽ ፺፱
## የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ አሰያየምና የሥራ ዘመን

፩· ዋና አስተዳዳሪ በወረዳው ምክር ቤት አብላጫ ድምጽ ባገኘው የፖለቲካ ድርጅት ወይም የፖለቲካ ድርጅቶች አቅራቢነት በምርጫ ይሰየማል።

፪· በዚህ ሕገ መንግሥት በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር የወረዳው

ዋና አስተዳዳሪ የሥራ ዘመን ለወረዳው ምክር ቤት የሥራ ዘመን ይሆናል።

## አንቀጽ ፴
## የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ ሥልጣንና ተግባር

፩. ዋና አስተዳዳሪ የወረዳው አስተዳደር ሥራ መሪ፣ የአስተዳደሩ ምክር ቤት ሰብሳቢና አስተዳዳሪ ነው

፪. ዋና አስተዳዳሪ ለወረዳ ምክር ቤትና ለዞኑ ዋና አስተዳዳሪ ተጠሪ ሆኖ፡-

ሀ) የወረዳውን አስተዳደር ይወክላል ፤

ለ) የወረዳውን አስተዳደር ምክር ቤት ይመራል፤

ሐ) የፌዴራሉንና የክልሉን ሕግጋት መንግሥታት ፤ ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ፕሮግራሞች በወረዳው ውስጥ በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል ፤

መ) የወረዳውን አስተዳደር ምክር ቤት አባላት ፤ ሌሎች ልዩ ልዩ ተቋማትና በሥሩ የሚገኙበትን ቀበሌዎች ሥራ በበላይነት ያስተባብራል፣ ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

ሠ) የወረዳው ማህበራዊ አገልግሎቶች፣ የኢኮኖሚያዊ ልማት ፕሮግራሞች እና እቅዶች ወቅቱን ጠብቀው መዘጋጀታቸውን ይቆጣጠራል፣ ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል፤

ረ) የወረዳው ነዋሪ ሕዝብ ሠላምና ደህንነት በአስተማማኝ ሁኔታ ይጠበቅ ዘንድ ሕግና ሥርዓትን እንዲያስከብሩ የተቋቋሙትን የፀጥታና የፖሊስ ኃይሎች በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

ሰ) ለወረዳው አስተዳደር ምክር ቤት፣ ለወረዳው ምክር ቤትና ለዞን አስተዳደር በየጊዜው ሪፖርት ያቀርባል ፤

ሸ) የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት አባላትን ለወረዳው ምክር ቤት በማቅረብ ያሾማል። ምክትል ዋና አስተዳዳሪው የምክር ቤት አባል መሆን አለበት።



www.abyssinialaw.com

ቀ) በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፺፱ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና አስተዳዳሪው የወረዳውን ምክር ቤት መሥራች ጉባዔ ይጠራል፤

በ) በወረዳው ምክር ቤትና በዞን አስተዳደር ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## አንቀጽ ፴፩
## የወረዳ ምክትል ዋና አስተዳዳሪ ሥልጣንና ተግባር

የወረዳው ምክትል ዋና አስተዳዳሪ ተጠሪነቱ ለዋና አስተዳዳሪውና ለወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት ሆኖ፦

፩. ዋና አስተዳዳሪው በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል።

፪. የወረዳው አስተዳደር ምክር ቤትና ዋና አስተዳዳሪው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## አንቀጽ ፴፪
## የወረዳ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት

፩. የወረዳ ዋና አስተዳደር ጽሕፈት ቤት በዋና አስተዳዳሪው ተመርጦ በሚመደብ አንድ የሥራ ኃላፊ ይመራል ።

፪. በዚህ ሕገ መንግሥት የርዕሰ መስተዳድሩን ጽሕፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር አስመልክቶ የተደነገጉት የወረዳውን ዋና አስተዳዳሪ ጽሕፈት ቤት በሚመለከት እንደ አግባብነታቸው ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል ።

## ምዕራፍ አሥር
## የቀበሌ አስተዳደር አደረጃጀትና ሥልጣን

## አንቀጽ ፴፫
## አደረጃጀትና ተጠሪነት

፩. የቀበሌ አስተዳደር የክልሉ የመጨረሻ መንግሥታዊ አስተዳደር

www.abyssinialaw.com

እርከን ነው ።

፪· የቀበሌ አስተዳደር የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፡—

ሀ) የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት፤

ለ) የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት ፤

ሐ) የቀበሌ ማኅበራዊ ፍርድ ቤት ።

አንቀጽ ፳፬

የቀበሌ ምክር ቤት

፩· የቀበሌ ምክር ቤት የቀበሌው ነዋሪ ሕዝብ ከፍተኛ የሥልጣን አካል ሆኖ ተቋቁሟል ።

፪· የቀበሌ ምክር ቤት አባሎች በቀጥታ በቀበሌው ነዋሪ ሕዝብ የሚመረጡ ይሆናሉ ። ተጠሪነታቸውም ለመረጠው ሕዝብ ነው።

አንቀጽ ፳፭

የቀበሌ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

የቀበሌ ምክር ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡—

፩· የበላይ የሆኑ የመንግሥት አካላት ከሚያወጧቸው ፖሊሲዎች ፣ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ጋር በማይቃረን መንገድ በአካባቢው ጉዳይ የአፈፃፀም መመሪያዎችን ያወጣል።

፪· ከምክር ቤቱ አባላት መካከል የቀበሌውን ዋና አስተዳዳሪ ፤ በምርጫ ይሰይማል ፤ የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት አባላትን ሹመት ያፀድቃል፤

፫· በቀበሌው ዋና አስተዳዳሪ ተመርጠው የሚቀርቡለትን የማኅበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች ሹመት ያፀድቃል ፤

፬· የበላይ በሆኑ የመንግሥት አካላት የሚሰጡትን የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማትና አስተዳደራዊ እቅዶችና ፕሮግራሞች ተቀብሎ በቀበሌው ውስጥ በሥራ ላይ የሚውሉበትን መርሃ ግብር ያወጣል፤ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

፭· ለቀበሌ ነዋሪ ሕዝብ የሚጠቅሙ ሌሎች ተጨማሪ እቅዶችን ያወጣል፤



ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል ፤

፮· የቀበሌውን ሕዝብ ለልማት ሥራና፣ የተፈጥሮ ሃብትን ልማት ፣ ጥበቃና እንክብካቤ የሚነሳሳበትን ሁኔታ ያመቻቻል ፤

፯· የቀበሌው ነዋሪ ሕዝብ ሠላምና ደህንነት መጠበቁንና ሕግና ሥርዓቱ መከበሩን ያረጋግጣል ፤

፰· የቀበሌውን ዋና አስተዳዳሪና ሌሎች ባለሥልጣናትን ለጥያቄ ይጠራል ፡ አሠራራቸውንም ይመረምራል ።

አንቀጽ ፳፮

የምክር ቤቱ አመራር

፩· የቀበሌ ምክር ቤት ከአባላቱ መካከል በሚመረጡ አፈ ጉባዔ እና ምክትል አፈ ጉባዔ ይመራል ።

፪· በዚህ ሕገመንግሥት ስለክልሉ ምክር ቤት አፈጉባዔ ሥልጣንና ተግባር አስመልክቶ የተደነገጉት ለቀበሌ ምክር ቤት አፈጉባዔ እንደአግባብነቱ ተፈጻሚ ይሆናል ።

፫· ምክትል አፈ–ጉባዔው በአፈ ጉባዔው ተለይቶ የተሰጡትን ተግባራት ያከናውናል ። አፈ ጉባዔው በማይገኝበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል ።

፬· በአፈ ጉባኤ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

አንቀጽ ፳፯

የምክር ቤቱ የስብሰባ ጊዜና የሥራ ዘመን

፩· የቀበሌው ምክር ቤት መደበኛ ስብሰባውን በወር አንድ ጊዜ ያካሂዳል።

፪· ከምክር ቤቱ አባላት ከሁለት ሦስተኛ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል ። የምክር ቤቱ ውሣኔ ስብሰባው ላይ በተገኙ የምክር ቤቱ አባላት የአብላጫ ድምጽ ይተላለፋል ።

፫· የቀበሌ ምክር ቤት የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል ። የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ከማብቃቱ አንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሂዶ ይጠናቀቃል ። የቀድሞው ምክር ቤት ሥራ ዘመን በተጠናቀቀ አሥራ አምስት ቀናት ውስጥ አዲሱ ምክር ቤት ሥራውን ይጀምራል

፮· ምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በማያደርግበት ወቅት አፈ ጉባኤልው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል። ከምክር ቤቱ አባላት መካከል አንድ ሦስተኛው የሚሆኑት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ከጠየቁ አፈ ጉባኤው ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት ።

## አንቀጽ ፲፰
## የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት

፩· የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት የቀበሌው ዋና አስተዳዳሪ ፣ ምክትል ዋና አስተዳዳሪና በቀበሌው ምክር ቤት በተጨማሪ ተመርጠው የሚሰየሙ በቀበሌው ውስጥ ከሚገኙ የማኅበራዊ እና አገልግሎት ሰጭ የመንግሥት ተቋማት ሠራተኞችና ኃላፊዎች አባላት የሚገኙ በትና የበላዩ በሆኑት አካላት የሚወጡ ሕጎች ፣ ደንቦችና መመሪያዎች አስፈጻሚ የበታች አካል ነው ።

፪· የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለቀበሌው ዋና አስተዳዳሪ፣ ለመረጠው የቀበሌ ምክር ቤትና ለወረዳው ወይም ከተማ አስተዳደር ይሆናል ።

፫· የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት በግልና በወል የቀበሌውን አስተዳደር ሥራ ይመራሉ ፣ ያስተባብራሉ ።

፬· የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት ለሚያሳልፏት ውሳኔና ለሚፈፅሙት ተግባር የጋራ ኃላፊነት አለባቸው ።

## አንቀጽ ፲፱
## የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

፩· የዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፲፰ ንዑስ አንቀጽ ፩ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ) የቀበሌው ምክር ቤት የሚነድፋቸውን የልማት እቅዶችና ፕሮግራሞች በቀበሌው ውስጥ በሥራ ላይ ያውላል ፣ የራሱን የልማት እቅዶች ይነድፋል፤ ለቀበሌው ምክር ቤት አያቀረበ ያስፀድቃል ፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል ፤



www.abyssinialaw.com

ለ) በቀበሌው ውስጥ የሚካሄዱ የማኅበራዊ አገልግሎቶች እቅዶች በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል ፣ ይቆጣጠራል ፤

ሐ) የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ ፣ እንክብካቤና ልማት ሥራ በከፍተኛ ደረጃ እንዲካሄድ ያደርጋል ፣ ሕዝቡንም ለልማት ሥራ ያንቀሳቅሳል፣ ያስተባብራል ፤

መ) የቀበሌው ሠላምና ፀጥታ እንዲጠበቅ ያደርጋል ፤

ሠ) በአካባቢው ለሚገኙት ቅርስ ቅርስ ተገቢውን ጥበቃና እንክብካቤ ያደርጋል ፣ በጥቅም ላይ ስለሚውሉበት መንገድም የበላዩ ለሆኑት አካላት ያሳውቃል ፤

ረ) በቀበሌው ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

፪· የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት የሥራ እቅዶቹን የሚነድፈው አፈፃፀማቸውን የሚከታተለው እና የሚገመግመው በየጊዜው እየተገናኘ ይሆናል ።

## አንቀጽ ፳
## የቀበሌው ዋና አስተዳዳሪ አሰያየምና የሥራ ዘመን

፩· የቀበሌ ዋና አስተዳዳሪ ከቀበሌው ምክር ቤት አብላጫ ድምጽ ባገኘው የፖለቲካ ድርጅት ወይም የፖለቲካ ድርጅቶች አቅራቢነት በምርጫ ይሰየማል።

፪· በዚህ ሕገ መንግሥት በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር የቀበሌ ዋና አስተዳዳሪው የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል።

## አንቀጽ ፳፩
## የቀበሌ ዋና አስተዳዳሪ ሥልጣንና ተግባር

፩· የቀበሌ ዋና አስተዳዳሪ ተጠሪነቱ ለቀበሌው ምክር ቤትና ለወረዳው ወይም ከተማው አስተዳደር ሆኖ የቀበሌው አስተዳዳሪና ሥራ መሪ ነው፤

፪· የቀበሌው ዋና አስተዳዳሪ ከዚህ በታች የተመለከቱት ሥልጣንና

ተግባራት ይኖሩታል፡—

ሀ) የቀበሌውን አስተዳደር ምክር ቤት ይሰበስባል፣ ይመራል፣

ለ) የበላዩ በሆኑት የመንግሥት አካላት የሚወጡትን ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና እቅዶች በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

ሐ) እጩ የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞችን በአስተዳደር ምክር ቤት አማካኝነት እንዲጣራ ካደረገ በኋላ ለቀበሌው ምክር ቤት አቅርቦ ያሾማል፣

መ) ለቀበሌው አስተዳደር ምክር ቤት ፣ ለቀበሌው ምክር ቤት፣ ለነዋሪው ሕዝብና ለተደራጀበት ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር በየጊዜው የሥራ ሪፖርት ያቀርባል፤

ሠ) የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት አባላትን ለቀበሌው ምክር ቤት በማቅረብ ያሾማል። ምክትል ዋና አስተዳዳሪው የቀበሌው ምክርቤት አባል መሆን አለበት፣

ረ) የዚህ ሕገመንግሥት አንቀጽ ፻፲ ንዑስ አንቀጽ ፪ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና አስተዳዳሪው የቀበሌውን ምክር ቤት መሥራች ጉባዔ ይጠራል፤

ሰ· በቀበሌው ምክር ቤትና በሚመለከተው ወረዳ አስተዳደር ወይም ከተማ አስተዳደር የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## አንቀጽ ፻፲፪
## የቀበሌ ምክትል ዋና አስተዳዳሪ ሥልጣንና ተግባር

የቀበሌ ምክትል ዋና አስተዳዳሪ ተጠሪነቱ ለዋና አስተዳዳሪና ለቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት ሆኖ፡—

፩· ዋና አስተዳዳሪው በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል።

፪· በቀበሌው አስተዳደር ምክር ቤትና በቀበሌው ዋና አስተዳዳሪ ተለይተው የተሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።



www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ ፻፲፫
## የቀበሌ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት

፩· የቀበሌ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት የአስተዳደር ምክር ቤቱ እና የምክር ቤቱ ሥራዎች በጣምራ የሚከናወኑበት ጽሕፈት ቤት ሆኖ ሊያገለግል ይችላል።

፪· የቀበሌውን ጽሕፈት ቤት በበላይነት የሚመራው የቀበሌው ዋና አስተዳዳሪ ሲሆን የምክር ቤቱ ሥራዎች ግን ይህንኑ ጽሕፈት ቤት በመጋራት በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፩፻፪ መሠረት አፈ ጉባዔና ዋና አስተዳዳሪ ፀሐፊ ተለይተው ይመራሉ፣ ይከናወናሉ።

## አንቀጽ ፻፲፬
## የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት

፩· የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት የቀበሌው ማህበራዊ የዳኝነት አካል ሆኖ በዚህ ሕገ መንግሥት ተቋቁሟል። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

፪· የማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፩፻፰ ንዑስ አንቀጽ ፫ ሥር በተደነገገው መሠረት የሚሾሙ ይሆናሉ።

## ምዕራፍ አሥራ አንድ
## የክልሉ ፖሊሲ መርሆዎችና ዓላማዎች

## አንቀጽ ፻፲፭
## ዓላማዎች

፩· ማንኛውም የመንግሥት አካል የፌዴራሉንና የክልሉን ሕግጋተ መንግሥታት፣ ሌሎች ሕጎችና ፖሊሲዎች በሥራ ላይ ሲያውል በዚህ ምዕራፍ በተመለከቱ መርሆዎችና ዓላማዎች ላይ መመስረት አለበት።

፪· በዚህ ምዕራፍ ውስጥ «መንግሥት» ማለት ደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግሥት ማለት ይሆናል።

## አንቀጽ ፻፲፮
## ፖለቲካ ነክ ዓላማዎች

፩· መንግሥት በዴሞክረሲያዊ መርሆዎች ላይ በመመስረት ሕዝቡ በሁሉም ደረጃዎች ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለበት።

፪· መንግሥት የብሔረሰቦችንና የሕዝቦችን ማንነት የማክበር፣ በዚህ ላይ በመመርኮዝ በመካከላቸው እኩልነትን ፣ አንድነትንና ወንድማማችነትን የማጠናከር ግዴታ አለበት ። በተለይ ደበልጥ በልማት ኋላ ቀር ለሆኑት ብሔረሰቦች ልዩ ትኩረት በማድረግ እኩልነታቸውን ማረጋገጥ አለበት።

## አንቀጽ ፻፲፯
## ኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎች

፩· መንግሥት ሁሉም የክልሉ ነዋሪዎች ባላቸው እውቀትና ሀብት ተጠቃሚ የሚሆኑበትን መንገድ የመየቀስ ኃላፊነት አለበት።

፪· የክልሉ ነዋሪዎች የኢኮኖሚ ሁኔታዎችን ለማሻሻል እኩል እድል እንዲኖራቸው ለማድረግና ሀብት ፍትሐዊ በሆነ መንገድ የሚከፋፈልበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለበት።

፫· መንግሥት በልማት ወደ ኋላ ለቀሩ ብሔረሰቦች ልዩ ድጋፍ ያደርጋል።

፬· የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ እንዳይደርስ መከላከልና አደጋው ሲደርስም ለተጎጂው እርዳታ በወቅቱ እንዲደርስ ማድረግ አለበት።

፭· መንግሥት መሬትንና የተፈጥሮ ሀብትን በሕዝብ ስም ይዞታው ሥር በማድረግ ለሕዝቡ የጋራ ጥቅም እንዲውሉ የማድረግ ኃላፊነት አለበት።

፮· የክልሉ ልማት ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ሲዘጋጁ ሕዝቡ እንዲሳተፍ ማድረግ አለበት። የሕዝቡን የልማት እንቅስቃሴዎች መደገፍ



www.abyssinialaw.com

አለበት።

፯· መንግሥት የሕዝቡን ዕውቀት፣ ጉልበትና ገንዘብ በማቀናጀት ፈጣን ልማት የሚረጋገጥበትን መንገድ መቀየስ አለበት። ሕዝቡ በክልሉ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ሚና እንዲኖረው ማድረግ አለበት። ስለሆነም ሕዝቡ ዕቅዶችንና ፖሊሲዎችን በመደገፍ ብቻ ሳይሆን በማስፈፀምና በመገምገም መሳተፍ አለበት።

፰· መንግሥት በኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ የልማት እንቅስቃሴዎች ውስጥ ሴቶች ከወንዶች እኩል የሚሳተፉበትን ሁኔታ የማመቻቸት ኃላፊነት አለበት።

፱· መንግሥት የሠራተኛውን ሕዝብ ጤንነት፣ ደህንነትና የኑሮ ደረጃ ለመጠበቅ መጣር አለበት።

## አንቀጽ ፻፲፰
## ማሕበራዊ ነክ ዓላማዎች

፩· የአገሪቱና የክልሉ አቅም በፈቀደ መጠን ሁሉም የክልሉ ነዋሪዎች የትምህርት፣ የጤና አገልግሎት፣ የንፁህ ውሃ፣ የመኖሪያና የምግብ በራዊ ዋስትና እንዲኖራቸው ያደርጋል።

፪· ትምህርት ከሃይማኖት ፣ ከፖለቲካ አመለካከቶችና ከባህላዊ ተፅዕኖዎች ነፃ በሆነ መንገድ ይካሄዳል።

## አንቀጽ ፻፲፱
## ባሕል ነክ ዓላማዎች

፩· የክልሉ መንግሥት መሠረታዊ መብቶችና ሰብዓዊ ክብርን እንዲሁም ዲሞክራሲንና ሕገ መንግሥቱን የሚጻረሩ ባህሎችና ልማዶች በእኩልነት እንዲጎለብቱና እንዲያድጉ የመርዳት ኃላፊነት አለበት።

፪· የተፈጥሮ ሀብቶችንና የታሪክ ቅርሶችን መጠበቅ የመንግሥትና የሁሉም የክልሉ ነዋሪዎች ግዴታ ነው።

፫· የክልሉ መንግሥት አቅም በፈቀደ መጠን ኪነ ጥበብን፣ ሳይንስንና ቴክኖሎጂን የማስፋፋት ግዴታ አለበት።

## አንቀጽ ፶፰
## የአካባቢ ደህንነት ጥበቃ ዓላማዎች

፩· መንግሥት ሁሉም የክልሉ ነዋሪ ንፁህና ጤናማ አካባቢ እንዲኖረው የመጣር ኃላፊነት አለበት።

፪· ማንኛውም የኢኮኖሚ ልማት እርምጃ የአካባቢውን ደህንነት የማያናጋ መሆን አለበት።

፫· የሕዝብና የአካባቢ ደህንነት የሚመለከት ፖሊሲና ፕሮግራም በሚነደፍበትና ሥራ ላይ በሚውልበት ጊዜ የሚመለከተው ሕዝብ ሃሳቡን እንዲገልጽ መደረግ አለበት።

፬· መንግሥትና የክልሉ ነዋሪዎች አካባቢያቸውን የመንከባከብ ግዴታ አለባቸው።

## ምዕራፍ አሥራ ሁለት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች
## አንቀጽ ፶፱
## የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ

፩· የፌዴራሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፺፫ ንዑስ አንቀጽ ፩/ለ/ እና በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፹፮ ንዑስ አንቀጽ ፯ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ማናቸውም የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም የሕዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ አውጥቶ ተግባራዊ ያደርጋል።

፪· የመስተዳድር ምክር ቤቱ የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ ባወጣበት በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ አፈ ጉባዔው የክልሉን ምክር ቤት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ማሳወቅና የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌውን ለምክር ቤቱ በማቅረብ ማስጸደቅ አለበት። ድንጋጌው በምክር ቤቱ ሁለት ሶስተኛ ድምጽ ተቀባይነት ካላገኘ ወዲያውኑ ይሻራል።

፫· የመስተዳድር ምክር ቤቱ ያወጣው የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ በክልሉ ምክር ቤት ተቀባይነት ካገኘ ሊቆይ የሚችለው ለስድስት ወራት ብቻ ይሆናል። ሆኖም የክልሉ ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ ድምፅ ሲወስን የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌውን በየአራት ወሩ እንዲታደስ ለማድረግ ይችላል።

፬· የመስተዳድር ምክር ቤት የክልሉ ምክር ቤት በአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ ሥር የሚያወጣቸው ደንቦችና የሚወስዳቸው እርምጃዎች በማናቸውም ረገድ በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፲፭፣ አንቀጽ ፲፮፣ አንቀጽ /፲፰/፩/ እና /፪/ አንቀጽ ፳፩ /፩/ አንቀጽ ፳፱/፩/ አንቀጽ ፳፭፣ አንቀጽ ፳፮/፩/ እና አንቀጽ ፴፱ የተቀመጡትን መብቶች የሚገድቡ መሆን የለባቸውም።

## አንቀጽ ፷
## የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ አፈጻፀም መርማሪ ቦርድ

፩· በክልሉ የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ በሚታወጅበት ወቅት የክልሉ ምክር ቤት ከአባላቱና ከሕግ ባለሙያዎች መርጦ የሚመድባቸው ሰባት አባላት ያሉት የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ መርማሪ ቦርድ ማቋቋም ይችላል። ቦርዱ የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌው በክልል ምክር ቤት በሚፀድቅበት ጊዜ ይቋቋማል።

፪· የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ መርማሪ ቦርድ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፦

ሀ) በአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ ምክንያት የታሰሩትን ግለሰቦች በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ይፋ ማድረግና የታሰሩበትን ምክንያት መግለፅ፤

ለ) በአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ ወቅት የሚወሰዱት እርምጃዎች በማናቸውም ረገድ ኢሰብዓዊ አለመሆናቸውን መቆጣጠርና መከታተል፤



www.abyssinialaw.com

ሐ) ማናቸውም የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ እርምጃ ኢሰብአዊ መሆኑን ሲያምንበት ርዕሰ መስተዳድሩ ወይም የመስተዳድሩ ምክር ቤት እርምጃውን እንዲያስተካክል ሃሳብ መስጠት፤

መ) በአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ እርምጃዎች ኢሰብአዊ ድርጊት የፈፀሙት ሁሉ ለፍርድ እንዲቀርቡ ማድረግ፤

ሠ) የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ እንዲቀጥል ለክልሉ ምክር ቤት ጥያቄ ሲቀርብ ያለውን አስተያየት ለምክር ቤቱ ማቅረብ።

## አንቀጽ ፻፳፫
## የክልሉ ዋና ኦዲተር

፩· የክልሉ ዋና ኦዲተር ተጠሪነቱ ለክልሉ ምክር ቤት ይሆናል።

፪· የክልሉ ዋና ኦዲተር የክልሉ መስተዳድር ተቋማትና የሌሎች መሥሪያ ቤቶች ሂሳቦችን በመቆጣጠር ለምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል።

፫· የክልሉ ዋና ኦዲተር የመሥሪያ ቤቱን በጀት በቀጥታ ለክልሉ ምክር ቤት አቅርቦ ያስፀድቃል።

፬· የዋናው ኦዲተር ሥልጣንና ተግባር በሕግ ይወሰናል።

## አንቀጽ ፻፳፬
## የሕገ መንግሥት ማሻሻያ ሀሳብን ማመንጨት

አንድ የሕገ መንግሥት ማሻሻያ ሀሳብ በክልሉ ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ ድምጽ ወይም ብሔረሰቦች ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ ድምጽ ወይም በክልሉ ከሚገኙት የዞን ወይም ልዩ ወረዳ ምክር ቤቶች ውስጥ አንድ ሦስተኛው በአብላጫ ድምጽ የደገፈው ከሆነ ለውይይትና ለውሣኔ ለመላው የክልሉ ሕዝብና የሕገ መንግሥቱ መሻሻል ለሚመለከታቸው ክፍሎች ይቀርባል።



www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ ፻፳፭
## ሕገ መንግሥቱን ስለማሻሻል

፩· ይህ አንቀጽ የሚሻሻለው በሚከተለው አኳኋን ብቻ ይሆናል፦

ሀ) ሁሉም የዞንና የልዩ ወረዳ ምክር ቤቶች የቀረበውን ማሻሻያ በድምጽ ብልጫ ሲያፀድቁት፣ እና

ለ) የክልሉ ምክር ቤትና የብሔረሰቦች ምክርቤት በሁለት ሶስተኛ ድምጽ የቀረበውን ማሻሻያ ሲያፀድቁት ነው።

፪· የዚህ ሕገመንግሥት ምዕራፍ ሁለትና ሶስት ድንጋጌዎች የሚሻሻሉት የፌደራሉ ሕገመንግሥት ምዕራፍ ሁለትና ሶስት ድንጋጌዎች ሲሻሻሉ ብቻ ይሆናል። ይህ ማሻሻያ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ መሠረት ይፀድቃል።

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ ከተጠቀሰው ውጪ ያሉት የሕገመንግሥቱ ድንጋጌዎች ሊሻሻሉ የሚችሉት በሚከተለው አኳኋን ብቻ ይሆናል፦

ሀ) የክልሉ ምክር ቤትና የብሔረሰቦች ምክር ቤት በጋራ ስብሰባ በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ሲያፀድቀው፣ እና

ለ) በክልሉ ከሚገኙት የዞንና የልዩ ወረዳ ምክር ቤቶች ውስጥ ሁለት ሶስተኛው በአብላጫ ድምጽ የቀረበውን ማሻሻያ ሲያፀድቁት ነው።

## አንቀጽ ፻፳፮
## ቀደም ሲል ስለተሾሙ ዳኞች

በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ሕገ መንግሥት አዋጅ ቁጥር 1/1987 ዓ·ም መሠረት የተሾሙ ዳኞች በዚህ ሕገ መንግሥት እንደተሾሙ ተደርጎ ይቆጠራል።

### አንቀጽ ፻፳፪
### ነባር ህጎች ስለመሥራታቸው

በክልሉ ውስጥ እስከሁን ድረስ ፀንቶ የሚሠራባቸው ነባር ሕጎች ደንቦችና መመሪያዎች ተሻሽሎ ከወጣው ከዚህ ሕገ መንግሥት ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

### አንቀጽ ፻፳፫
### የመጨረሻው ሕጋዊ ዕውቅና ቅጅ

የዚህ ሕገ መንግሥት አማርኛው ቅጅ የመጨረሻው ሕጋዊ ዕውቅና ያለው ሰነድ ነው።



www.abyssinialaw.com

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE REVISED CONSTITUTION, 2001, OF THE SOUTHERN NATIONS, NATIONALITIES AND PEOPLES REGIONAL STATE

Whereas, it is found necessary to indicate particularly the separation of power, and needs to be transparent and efficient of state organs; and proclaim, the existing Constitution of the Southern Nations, Nationalities and Peoples' Regional State, which consulted upon and ratified through elected representatives of the Peoples of the Region, on 22nd day of June, 1995;

Now, therefore, in accordance with power entrusted to it under Article 49 sub-Article 3(a) and Article 102, of the Constitution of the Southern Nations, Nationalities and Peoples Regional State, it is thereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

   This proclamation may be cited as the ''Revised Constitution, 2001, of the Southern Nations, Nationalities and Peoples Regional State Proclamation NO.35 2001."

2. *Approval*

   The revised Constitution, 2001, of the Southern Nations, Nationalities and Peoples' Regional State has approved after deeply assessed, the provisions, and contents of the Constition of the Sothern Nations, Nationalities and Peoples' Regional State Proclamation NO. 1/1995.

3. *Efflctive Date .*

   The Proclamation shall come in to force as of the 12th day of November, 2001.

Done at Awassaa, this 12th day of November, 2001

Hailemariam Desalegn
Chief Executive of the
Southern Nation, Nationalities
and Peoples' Regional State